# ዴሞክራሲያዊ ትግል በኢትዮጵያ

## ብርሃኑ ነጋ

### 1. መግቢያ፤

እለቱ ግንቦት 21 1990 ዓም ነው:: በአድአ ወረዳ በሚገኝ አንድ የቀበሌ ገበሬ ማሕበር ውስጥ ፤ አቶ ብሩ ማሞ በ85 አመታቸው እቤታቸው ቁጭ ብለው፤ ከሁለት ወንድ ልጆቻችው ጋር እየተጫወቱ ነበር :: አንደኛው ልጃቸው ጫላ፤ በአነስተኛ ንግድ ላይ የተሰማራ ስለሆነ የተለያየ ቦታ ሲንቀሳቀስና ሲነግድ ቆይቶ ከብዙ ወራት በኋላ ነበር ወደ አባቱ ቤት የተመለሰው:: ሁለተኛው ልጃቸው ቱሉ ከእርሳቸው ጋር አብሮ የሚያርስ ( ግን የራሱ ቤተሰብ የመሰረተ ) ሲሆን፤ አቶ ብሩና ልጃቸው ቱሉ ከእርሻቸው በተጨማሪ የአከባቢያቸው ወጌሻ በመሆን ማሕበረሰባቸውን ያገለግላሉ:: ከ1990 ዓም ቀደም ብሎ አቶ ብሩ ትንሽ እርጅናው ስለተጫናቸው የወጌሻነቱን ሥራ ለልጃቸው ሙሉ በሙሉ ቢያስተላልፉም፤ ሰውነታቸው ጠንካራ ስለሆነ እርሻውን ሙሉ ለሙሉ አላቆሙትም ነበር::[1] በዚያች የተረገመች ቀን ከልጃቸው ጋር እየተጫወቱ እያሉ ነበር ቤታቸው በፖሊስ የተከበበውና እጃቸውን እንዲሰጡ የተጠየቁት:: ፖሊሶቹ ሲከታተሉት የነበሩትና ሊያስሩትም የመጡት ልጃቸውን ጫላን ነበር:: ሁኔታው ግራ አጋብቷቸው ፖሊሶቹ ምን እንደሆነ የሚፈልጉት ሲጠይቁ፤ያገኙት መልስ ጫላን ለጥያቄ እንደሚፈልጉትና እርሳቸውንና ሌላ ልጃቸውን ቱሉን ግን እንደማይፈልጓቸው፤ ጫላን ግን ከአዲስ አበባ በመጣ ትእዛዝ እንደሆነ የሚፈለገው፣ ግን ዝርዝሩን እንደማያውቁ፣ ለማንኛውም ግን ሶስቱም አብረው አዳማ ቢሄዱና አቶ ብሩና ቱሉ አስፈላጊ ከሆነና የልጃቸውን ተግባር የሚያውቁ ከሆነ፤ የማስተባበያ ምስክር ሰጥተው ልጃቸውን ይዘው እንደሚመለሱ ተነግሯቸው፤ በፖሊስ ፒካፕ መኪና አባትና ሁለት ልጆች ተጭነው ወደ አዳማ ፖሊስ ጣቢያ ይወሰዳሉ:: አዳማ ደርሰው ጊዚያዊ እስር ቤት እንዲቆዩ ይደረግና በሁለተኛው ቀን አቶ ጫላን የሚፈልጉት የፌዴራል ደህንነት ሰዎች አዳማ ድረስ መጥተው ጫላ በኦነግ አባልነት እአንደሚጠረጠርና ለዝርዝር ምርመራ አዲስ አበባ መሄድ እአንዳለበት፤ አቶ ብሩና ልጃቸው ቱሉ ተጠርጣሪ ባይሆኑም ለማንኛውም ለጥያቄ አብረው አዲስ አበባ እአንዲሄዱ ወስነው ሁሉንም ይዘዋቸው ወደ ማዕከላዊ እስር ቤት ያስገቧቸዋል:: ከዚህ በኋላ ስለሆነው ነገር አቶ ብሩ ብዙም የሚያውቁት ነገር የለም :: ለረጅም ወራት በማዕከላዊ ከቆዩ በኋላ የኦነግ አሸባሪ ቡድን አባላት ናቸው በሚል ክስ ተመስርቶባቸውና የዋስ መብት ተከልክለው ወህኒ ይወርዳሉ:: በተለያዩ ምክንያቶች በአማካኝ አመት በሚወስድ የቀጠሮ መንተት ጉዳዩ ብይን ደረጃ ላይ ከስምንት አመት ግድም በኋላ በ1998 ዓም ይደርሳል:: በዚህም ጊዜ ውስጥ በተለይ በሁለቱ ተከሳሾች ላይ ጫላን እገዛ አባቱ ቤት ደበቁ ከሚል ውጭ ኦነግ ናቸው፤ ወይንም ከኦነግ ጋር በመተባበር ይህንን ድረጊት ፈጽሙ የሚል አንድም የሰውም ሆነ የሰነድ ማስረጃ አልቀረበባቸውም:: ለነገሩ በልጃቸው በጫላም ላይ የቀረበው ማስረጃ ምንም ወንጀለኛነትን የሚያሳይ አልነበረም:: ለማንኛውም በብይኑ ግዜ ( ሀምሌ 1998 ) ፍ/ቤቱ አቶ ብሩንና ልጃቸውን ቱሉን ከስምንት አመት እስር በኋላ ምንም ማስረጃ ስላልቀረበባቸው በሚል በነጻ አሰናበተቸው:: ጫላን ደግሞ የክሱን አንቀጽ በመቀየርና እስከ 15 ዓመት ጽኑ እስራት በሚያስቀጣ አንቀጽ እንዲከላከል ይበየንበተል:: ነጻ የተባሉት አባትና ልጅ ከላይ ከላዩ በመለቀቃቸው ፈጣሪያቸውን እያመሰገኑ ውስጣቸው ግን እየበገነና ምናልባትም ይህች ሃገር እንዴት ሃገራችን ነች እዕንላለን፣ ኦሮሞ በመሆናችን ብቻ እንደዚህ እየተቀጣን? እያሉ ወደ ትውልድ መንደራቸው

---

[1]. በነገራችን ላይ የአቶ ብሩ ጥንከሬ በእስር ቤትም ውስጥ የተመሰከረላቸው ነው :: ሁሌም ሰውን ሰላም ሲሉ በቦክስ ጎሸም እያደረጉ ሰለሆነ ፤ የእስር ቤት ቅጽል ስማቸው ጄኔራል ነው :: ከእስር ቤት በ93 አመተቸው ሲወጡ ጥንከሬያቸው ሙሉ ለሙሉ አልከዳቸውም ነበር ::

ይመለሳሉ:: ጫላ በመጀመርያ ላይ የቀረበበት ማስረጃ ምንም መሰረት የሌለው፤ ክሱም የተፈበረከ መሆኑን ፍጽም እዕርግጠኛ ሆኖ፤ የመከላከያ ምስክሮቹን አቅርቦ ክሱን ለመከላከል አስቦ ነበር:: ሆኖም በአስር አመት የእስር ህይወት ያገኘው የህግ እውቀትና የሌሎችም እዕሰረኞች በተመክሮ የዳበረ ልምድ ታክሎበት እከላከላለሁ የሚለውን ሃሳቡን ቀየረ:: እከላከላለሁ ካለ ገና ለብዙ አመታት እንደሚተስር፤ አልከላከልም ካለ ግን ፍ/ቤቱ ተከላከል ባለው አንቀጽ ሊፈረድበት የሚችለውን የመጨረሻ ከፍተኛ የ15 አመት ቅጣት ቢበየንበትም እንኳን የ15 ዓመት እስሩን እየጨረሰ ስለሆነ (በአመክሮ 5 አመት ስለሚቀነስለት ) በጥቂት ወራት ግዜ ነጻ ዕንደሚወጣ በተመከረው መሰረት አልከላከልም በማለትና አስራ አምስት ዓመት ተፈርዶበት ተለቀቀ::[2]

ስዩ አብረሀ ከመላ ዘመዶቹ ጋር ከታሰረ ጀምሮ በእስር ለማቆየት መንግስት ያልፈነቀለው ድንጋይ የለም:: በህግ አወጣጥ ታሪክ ወደር በማይገኝለት ፍጥነትና መሰረታዊ የሆነውን የህገ-መንግስት መርህ በመጣስ በአንድ ቀን (ብርቱካን የዋስ መብት ስለፈቀደችለት)፣ በሙስና የተከሰሰ ሰው የዋስ መብት አይፈቀድለትም የሚልና፣ የአዲስ አበባ ሕዝብ የስዬ ህግ፣ እያለ የሚጠራውን ህግ አውጥቶ መንግስት በስራ ላይ አዋለ:: ዋና አላማውም ቢያንስ እስከሚፈረድበት በዕስር ላይ ለማቆየት ነበር:: ከስድስት አመት እስር በኋላ መንግስት በአንድ ምክንያት ወይም በሌላ ስዬን ከዕስር ለመፍታት ሲወስን፤ ፍ/ቤቱ ስዬን ጥፋተኛ ብሎ ስድስት አመት የፈረደበት ጉዳይ የሰው ልጅ ህይወትን የሚመለከት አሳዛኝ ጉዳይ ባይሆን ኖሮ በጣም አስቂኝ ነበር:: ምክንያቱም ወንጀሉ ምን እንደሆነ በፍጽም ግራ የሚገባ ነው:: ስዬ የኤፈርት ስራ አስኪያጅ ሆኖ አይቬኮ ከሚባለው የጣሊያን ኩባኒያ (ኢትዩጵያ ውስጥ ከአለውና የመንግስት አክሲዮን ከአለበት አይደለም) ለኤፈርት ብዙ የጭነት መኪናዎች ሲገዙ ጠቀም ያለ ቅናሽ በድርድር አግኝቷል:: ይህ ከሆነ ከሁለት አመት ግድም በኋላ የሱ ወንድምና ሌሎች ባለ ሀብቶች መንግስት ለነዳጅ ትራንስፖርት ብዙ የመኪና ባለሀብቶች እንዲገዙ በወተወተው መሰረት ተሰባስበው (ቅናሽ ለማግኘት) በዛ ያለ መኪና ጣልያን ካለው አይቬኮ ይገዛሉ:: ስለዚህም ሁሉም አንድ አይነት ቅናሽ ከኩባንያው ያገኛሉ:: ዕንግዲህ ወንጀሉ ስዬ ያለውን ስልጣን ተጠቅሞ ከውጭ ኩባንያ ለወንድሙ ቅናሽ አስገኘ ነው:: ኩባንያው የጣልያን ነው:: የኢትዮጵያ መንግስት ከኩባንያው የሚያገኘው ምንም ጥቅም የለም:: እንዲያውም ብዙ ቅናሽ ኢትዮጵያውያን ካገኙ ሃገሪቱ ያንኑ ያህል የውጭ ምንዛሪ ታድናለች:: ስዬ በምን መልኩ፣ የትኛውን ስልጣኑን ተጠቅሞ፤ ማንን ገፋፍቶ ይህንን ቅናሽ እንዳስገኘ የተጠቀሰ ማስረጃ የለም:: ለዚህም ወንጀል 6 አመት በዕስር ቆየ::

የፕሮፌሰር አስራትን ስቃይ እዚህ ያላችሁት ብዙዎቻችሁ ታውቁተላችሁና ብዙ መተንተን አያስፈልግም:: እሳቸውም በፖለቲካ ባላንጣነታቸው ተፈርጀው፣ የፈጠራ ክስ ተምስርቶባቸው፣ የውሸት ምስክር ተደርድሮባቸው ባልሰሩት ስራ ለአመታት ተስረዋል:: እንደ ስዬ ወይም እንደ አቶ ብሩ ግን እድለኛ ባለመሆናቸው የክሱን ድራማ ሙሉ ትዕይንት ሳያዩ በዕስር ቤት ከተጠናወተቸው ህመም ማገገም ባለመቻላቸው ሕይወታቸው አልፏል:: የሃገራችን እስር ቤቶች አፍ አውጥተው ቢናገሩ ከዚህም የከፉ ብዙ በጣም ብዙ አሰቃቂና ኢፍተሃዊ ድርጊቶች በሃገራችን ታይተዋል:: አሁንም በገፍ እየተፈጸሙ ነው::

---

[2] በፍርድ ቤት ተከራክሬ እውነቱን አወጣለሁ የሚል እምነት ( በተለይ ትንሽም ፖለቲከ ነክ ከሆነ ) በአሁኑ ጊዜ በአገራችን የለም :: ከፓርላማ ውጭም ፍ/ቤት ፍትህ ይሰጠኛል ተብሎ ሳይሆን የመውጫውን ቀልጣፉ መንገድ መፈለግ ነው ተመራጩ እስትራተጂ :: አንድ በመሬት ማጭበርበር የተከሰሰ ነጋዴ በፍጹም ያልሰራሁትን ወንጀል አላምንም ብሎ ከአስር አመት በኋላ አሁንም በእስር ሆኖ ክረክር ላይ ነው :: በእርግጥ የውሸት ከርታ አሰርተው ያጭበረበሩት ሌሎች ነጋዴዎች ድርጊታቸውን አምነው የሶስት አመት ፍርድ ተፈርዶባቸው ከእስር ከወጡ ሰባት አመት አለፋቸው :: በ1998 ሀምሌ ላይ ይህ ሰው መቼ ነው የሚፈረድብህ ስለው አሁንስ ሰለቸኝ ዳኛዋን በሚቀጥለው ቀጠሮ አጥፋቻለሁ ፍረጂብኝ እላታለሁ ብሎ ነበር :: እስከሁን እሱንም አላገኘውም ::

እነኚህን ሶስት የታወቁና ያልታወቁ የፍርድ ሂደቶች በዚህ ንግግር መግቢያ ላይ የጠቀስኳቸው ያለምክንያት አይደለም:: ይህ ንግግር የሚያጠነጥንባቸው ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮችን ከወዲሁ አስጨብጬ ለማለፍ ነው:: የመጀመሪያው የሃገራችን መሰረታዊ የፖለቲካ ችግር ፍትህ አልባነት መሆኑን ለማስረገጥና ፍትህ በሌለበት ወይም ፍትህ በጊዜው ጉልበተኞች እንደተፈለገ በሚረገጥበት ሃገር ዘላቂ የሆነ የፖለቲካ ማህበረሰብ አለ ለማለት እንደማይቻል ለማመላከት ነው:: ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርአት መነሻውና መሰንበቻው መድረሻውም በፍትህ ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ዕኩልነት መመስረት መሆኑን ለአንድ አፍታም ዕንዳንዘነጋው ለማሳሰብ ነው:: ሁለተኛው በሃገራችን ፍትህ አልባነት ጥቂት ግለሰቦች ወይም የባህል ስብስቦች ወይም ብሄር ብሄረሰቦች ላይ ያነጣጠረ ችግር ሳይሆን ጥቂት የስልጣን ጥመኞችና ከዚህ ከስልጣን በሚመጣ ጥቅም የማመዛዘን ችሎታቸውን ያጡ ጥቂት አድርባዮችን ካልሆነ በስተቀር ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የሚመለከትና በአስቸኳይ መፍትሄ ካልፈለግንለት አንዳችንን ከሌላችን ሳይለይ ሁላችንንም በአንድ ላይ ሊያጠፋ የተዘጋጀ አደገኛ መርዝ መሆኑን ተረድተን በዚህ ጉዳይ ዙሪያ በአስቸኳይ ተሰባስበን መፍትሄ መሻት እንዳለብን ለመግጸን ነው:: እዚህ ዝርዝር ውስጥ ከመግባቴ በፊት ግን አንድ ሁለት የምስጋና ቃላት ልወርውር::

ጥቅምት 22 ቀን ኢህአዴግ ቅንጅትን እንደ ፖለቲካ ድርጅት ሊያጠፋ ወስኖ አመራሩን፣ አባላቱንና በሺዎች የሚቆጠሩ ደጋፊዎቹን ሲያስር፣ ሰብስቦ ያሰራቸውን ሰዎች በተለይ የአመራር አበላት ለሱ በስልጣን መቆየት አደገኛ መሆናቸውን ከማመኑ በስተቀር ይህ እርምጃው በህዝብ ስነልቦና ላይ ሊተው ስለሚችለው ጠባሳ ብዙም የተጨነቀ አለመሆኑን ከድርጊቶቹ መረዳት አያዳግትም:: ወጣቶች በብዛት ያሉበትን ያክል፣ ብዙ አዛውንቶች፤ በጥሩ ጤንነት ላይ የሚገኙ ያሉበትን ያህል፣ ጤናቸው የታወከ ከፍተኛ የህክምና ክትትል የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ነበሩበት:: ታምመው ከተኙበት አልጋ አንስቶ ያሰራቸው አዛውንቶች አንደነበሩም ይታወቃል:: የዕስር ቆይተቸው ከላይ እንደጠቀስኳቸው ሌሎች የፍትህ እጦት ሰለባዎች በጣም ቢራዘም ኖሮ ሁሉንም በሕይወት ለማየት ያለን እድል አጠራጣሪ ነበር:: ስለዚህም ነው በመጀመሪያ መቅረብ ያለበት ምስጋና (በቀውሱ ጊዜ የተጨፈጨፉትን ወገኖቻችንን ለአንድም ሰኮንድ ሳንረሳ) በዕስር ከገባነው ውስጥ ምንም ሰው ሳናጣ በተለይ ለዚህች ሃገር ባለውለታ የሆኑ አዛውንቶች በህይወት እንዳሉ ይህ የዕስር ቅጣት ማብቃቱና ይህም እንዲሆን ላስቻሉት ሁሉ ሊሆን የሚገባው:: ከታሰሩት አዛውንቶች ውስጥ ( ወይም ወጣቶች) አንድም ሰው ዕንኳን አጥተን ቢሆን ኖሮ በማህበራችን ላይ የሚያደርሰው ጸጸትና ይህም ሊያስከትል ይችል የነበረው ማህበራዊ የስነ ልቦና ጠባሳ ቀላል አይሆንም ነበር:: ይህ የሆነበት ግን በዋነኛነት የዕስር ጊዜያችንን (አሁንም እረጅም ቢሆንም) አደጋ ሊያስከትል እስከሚችል ባለመቆየቱ ነው:: ለዚህ ደግሞ ብዙ በጣም ብዙ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያን ያልሆኑ የዴሞክራሲና የፍትህ ወገንተኞች የጋራ ትግል ውጤት ነው:: የሚያደርጉት ጨንቋቸው ጠዋት ማታ በየጸሎት ቤቱ ፈጣሪያቸውን ሲማጸኑት የነበሩት የኢትዮጵያ እናቶችና አባቶች፣ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ « መሪዎቻችን ይፈቱ» እያሉ በዚያ ሁሉ አፈናና ጭፍጨፋ መሃል በየትምህርት ቤቱ ከጨካኝ ፖሊስ ሃይሎች ጋር ፊት ለፊት ተጋፍጠው በአሰቃቂ ሁኔታ የተቀጠቀጡት ወጣት ተማሪዎች፣ በ30 ብር ነጻነታችንን እናገኝ ብለው በሩጫ ውድድር ጊዜ እኛ እንድንፈታ ድማጻቸውን ያሰሙ ጎልማሳ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ምስጋናና ክብር ይገባቸዋል::

ከቀጥታ አፈና እርቃችሁ የምትገኙ፣ እናንት በውጭ የምትገኙ ኢትዮያውያን ወገኖቻችን፣ የክረምት ብርድ የበጋ ጸሃይ ሳይበግራችሁ፣ የኛንም ሆነ የአገራችሁን ስቃይ ለአለም ህዝብ ለማሳወቅ የሰራችኋቸው የሎቢ ስራዎች፣ ያደረጋችኋቸው ስልፎችና ለዕስረኛ ቤተሰቦች እንዳይቸገሩ ደክማችሁ

ካገኛችሁት ገቢያችሁ ቀንሳችሁ እኛና ቤተሰቦቻችን እንዳንራብ በአገር ውስጥ ያለውም የዴሞክራሲ ትግል እንዳይቀዘቅዝ ያደረጋችሁት አስተዋጾኦ በፍጹም የማይረሳ፣ በዕጅጉ ያኮራን ነውና በሁላችንም ስም ምስጋናችን ይድረሳችሁ።

በሃገራችን ምርጫ ሲሰረቅ፣ የተጀመረው የዴሞክራሲያዊ ሂደት ተረግጦ በፍጹም አምባገነንት ሲተካ፣ የንጹሃን ደም በየአደባባዩ ሲፈስ «ድሮስ ከአፍሪካ ምድር ምን ይጠበቃል» በሚል ንቀትና ጨለምተኛነት ጉዳዩን ረስቶ ወደ ሌላ የአለም ችግር ከመዞር ወይም ደግሞ ምንም ሆነ ምን፣ ሰብአዊ መብት ተረገጠ አልተረገጠ የእኛ ተግባር ካለው መንግስት ጋር መነገድ ወይም ለእኛ የጥቅም ሸሪክ እንዲሆን ማበረታት ነው» በሚል ቅጥ ያጣ ግለኛነት ሳይሸነፉ የኢትዮጵያን ጉዳይ ጉዳያቸው ብለው አስከመጨረሻው አብረው የቆሙትን እንደ አና ጎሜዝ፣ ዶናልድ ፔይንና፤ ክሪስቶፎር ስሚዝን የመሳሰሉ የአውሮፓና የአሜሪካ ፖለቲከኞች እንዲሁም የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶች ሁሌም በላውለታዎቻችን ናቸውና መቸም አንረሳቸውም።

እናንተን ሁሉ የምናመሰግናችሁ ግን በጊዜው ከስር እንድንወጣ ላደረጋችሁት አስተዋጽኦ ብቻ አይደለም። በእስር ላይ እያለን የምታደርጉትን የተለያየ እንቅስቃሴ በተለያዩ የብዙሃን መገናኛዎች ስንሰማ ይሰማን የነበረው ጥንካሬ፣ ይሰጠን የነበረው መጽናናት በቀላሉ የማይመነዘርና በጤና ለመውጣታችን ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረገ መሆኑን ስለምናውቅ ነው። እናንተም ይህን ልትረሱት አይገባም። የወህኒ ቆይታ ትልቁ ጥያቄ « ተረሳን ወይ?» የሚለውና ይህ ስጋት የሚያመጣው ሃዘን ነው። ላላፉት 21 ወራት ግድም የእስር ቆይታችን ለአንድም ቀን እንኳን አለመረሳታችንን ስናውቅ ይሰጠን የነበረው የልብ ኩራት በጥቂት ቃላት የሚገለጽ አይደለም። እኛ እስር ላይ ሳለን በጋራ የቆምንለት የዴሞክራሲ ትግል በኢህአዴግ ቅጥ ያጣ አፈና አለመቆሙ እንዲያውም ከእዚህ በፊት ከዳር ቆመው ሁኔታዎችን ይመለከቱ የነበሩ ብዙ ኢትዮጵያውያን ይህንን የዴሞክራሲ ትግል በስፋት መቀላቀላቸው፣ ትግሉ ጥቂት መሪዎችን በማሰር የማይቆም መሆኑን ማሳየቱ በእርግጥም እስራታችንን ከምትገምቱት በላይ ቀላል እንዲሆን አድርጎታል። ይህ ማለት ሁሉም ነገር አልጋ ባልጋ ነበር ማለት አይደለም። በትግላችሁ የኮራነውን ያህል፣ ባለመረሳትችን የተጽናናነውን ያህል፣ የዴሞክራሲ ትግሉን ብዙ ኢትዮጵያውያን በመቀላቀላቸው ተስፋችን የለመለመውን ያክል፣ አንዳንዴ በዴሞክራሲ ትግል ውስጥ በሚገኙ ሃይሎች መሃል የነበረውን ሽኩቻ ስንሰማ፣ በወገን ሃይሎች መሃል የሚሰነዘሩትን የጥላቻ ሃይለ ቃሎች ስናዳምጥ፣ ከልብ ማዘናችንና ልባችን መሰበሩን፣ ይህ አይነቱ የወንድማማች ጸብ ደግሞ ትግሉን በቅርብና በንፅህና እንዲሁም በከፍተኛ ጥርጣሬ የተቀላቀሉትን ብዙ ሃይሎች ከፓለቲካ እንዲሸሹ ለማድረግ ያለውን አቅም በመረዳት ስለወደፊቱ ስንሰጋ መክረማችንን ብደብቃችሁ ከእውነቱ ያርቀኛል እና በጣም ከትልቁ ምስጋና ጋር ይህችን ትንሽዋንም ሀዘናችንን ገልጬ በማለፌ በጣም አትከፉም ብዬ አምናለሁ። ለማንኛውም ለመግቢያ ያክል ይህንን ያህል ከአልኩ ዛሬ አተኩራለሁ ወዳልኳቸው ዋና ዋና ነጥቦች በቀጥታ ልለፍ።

**2. አጭር የታሪክ ጉዞ፤**

በዛሬው እለት በአብዛኛው መናገር የምፈልገው ስላለፈው ሳይሆን ስለወደፊቱ ነው። የወደፊቱ ደግሞ ብዙ በጥንቃቄ እና በብልህነት ማለፍ የሚገባን መሰናክሎች የተደቀኑበት አደገኛ መንገድ ቢሆንም፤ መድረሻችንን በግልጽ ለማዬት እስከቻልን ድረስ እና  አይናችንን ከዚህ ግባችን፤ማለትም የተባበረችና የበለጸገች እውነተኛ ዲሞክራሲያዊት ኢትዬጵያን መገንባት፤ለአንድ አፍታም እስካላነሳን ድረስ

ከመቼውም ጊዜ በላይ ይህንን ግባችንን ለመምታት የሚያስችለን ሁኔታ ላይ ነንና ያለነው እዚያው እንደምንደርስ ለአንድ አፍታም እንኳን ጥርጣሬ ሊገባን አይገባም ። ጥያቄው እንዴት እዚያ እንደርሳለን እና መቼ እዚያ እንደርሳለን የሚለው ነው። ዛሬ በተለይ መወያዬት የምፈልገው እንዴት እዚያ እንደርሳለን? በሚለው ላይ ነው ።

ይህ ማለት አሁን ባለንበት ሁኔታ እና በግባችን መሀል ያለውን ጊዜ በሚመለከት ግባችንን ማእከል አድርገን እንዴት መጓዝ እንዳለብን ጥቂት ሀሳቦችን ለመሰንዘር ነው። ይህን ለማድረግ እንዲረዳን ለመንደርደሪያ ያክል በመጀመሪያ በአጭሩ ከዚሁ ጋር በተገናኘ የራሳችንን ማለትም የቅንጅት አመራር ስለ ወደፊቱ ግባችን የነበረውን እይታ እና በተለይ በምርጫው እና በእኛ መታሰር መሀከል በነበረው ጊዜ ከወሰንናቸው እና ለእዚህ ውይይት የተለየ ጥቅም አላቸው የምላቸውን ቁም ነገሮች ላነሳሳ ።

በመጀመሪያ በግልጽ ከታወቀው እንጀምር። ፓርላማ ለመግባት አስፈላጊ ናቸው ያልናቸውን ስምንት ነጥቦች ለማቅረብ ሁለት ቀናት የፈጀ ውይይት አድርገን በሙሉ ድምጽ ስንወስን ውሳኔያችን አመራሩን ሰእስር ሊዳርግ እንደሚችል ሙሉ ለሙሉ እርግጠኛ ነበርን ለማለት እንኳን ባይቻል ከሞላ ጎደል ውጤቱ ወደዚያ ሊያመራ እንደሚችል አውቀን ነበር ። በርግጥ ይህንን የማሰር አማራጭ ኢህአዴግ ሲወስድ ያመንገድ ሊያስከትል የሚችለውን ዘላቂ ውድቀት ( ለእራሱ ለኢህአዴግም ሆነ ለሀገሪቱ ) በመረዳት ከዚያ የተሻለ አማራጭ እንዳለ እንዲያይ እና ይህንንም አማረጭ በቀላሉ እንዲዋጥለት ለማድረግ መጓዝ አለብን ብለን ያመነውን የማለሳለስ እርምጃ በሙሉ ወስደናል ። ለዚህም ነው ለምሳሌ ምርጫውን እንዳጭበረበረ እና እንደሰረቀ እያወቅንም የ299 መቀመጫዎችን ጥያቄ እያመመንም የተውነው ። የዚያ ውሳኔ አላማ ዘላቂ ግባችንን በተቻለ መጠን በአነስተኛ ዋጋ ለማግኘት እስከቻልን ድረስ በስልት ደረጃ መምረጥ ያለብን እሱን ነው የሚል ነበር ። በኢህአዴግ በኩልም ከስልጣን በኋላ ህይወት አለ ብለው የማያምኑ እና ይህ ያለተገደበ ስልጣናቸው እንዳይነካባቸው የሚቃወማቸውን ሁሉ ለማጥፋት ቆርጠው የተነሱ ያሉበትን ያህል ቢያንስ የራሳቸውን ዘላቂ ጥቅም የሚያውቁና የፖለቲካ ግጭቱን በብሄራዊ እርቅ እና በድርድር ወደ ተለሳላሰ ማረፊያና እውነተኛ ዲሞክራሲ ለመውሰድ የሚሹ ሀይሎች በውስጣቸው ቢኖሩ፤ በመሀላቸው ለሚደረግ ክርክር ስንቅ ይሆናቸዋል የሚል የመጨረሻ ደቂቃ ተስፋ በመሰነቅም ነበር፤ ይህንን የተለሳለሰ አቋም የቅንጅቱ አመራር የያዘው ። ያም ሆኖ ግን ግጭት የሚፈልጉ የስልጣን ሱሰኞች የበላይነቱን ይዘው አገሪቱን ወደ ከፋ ግጭት፤ የቅንጅት አመራርንም ወደ እስር ከአለፈም ወደ ሞት ለመዳረግ የክፋት ችሎታውም ቁርጠኝነቱም ያላቸው ሀይሎች ለጊዜው ሊያሸንፉ እንደሚችሉ በደንብ አስልተን ነበር ።

ታዲያ ይሄንን እያወቅን ለምን ያንን ውሳኔ ወሰንን? ለምን እንደ አንዳንዶች በመጨረሻው ሰአትም እንኳን ስልታዊ ማፈግፈግ አድርገን፤ ፓርላማ ገብተን ጊዚያችንን አንጠብቅም ነበር? በመታሰር የሚገኝ ጥቅም አለ ብለን ነው? ወይንስ አቶ መቀስ እንደሚሉት ፈረንጆች ወይም አበሾች ከእስር ያስልጥሉናል ብለን ነው? የኋለኛው እንዳልሆነ እኛ ብቻ ሳንሆን አቶ መለሰም ያውቁታል ። እሳቸው እንዳሉትም ለእኛ በግልም በፈረንጆቹም ፊትም እየተኩራሩ ነግረውናል። አቶ መለስ የላኩዋቸው ሴትዬም ከአቶ መለሰ በተላኩት መሰረት በተደጋጋሚ ነግረውናል። አቶ መለስንም ሆነ ሴትየዋን ያበሳጫቸውም ይሄንን ሁሉ ማስፈራርያ ለመቀበል አለመቻላችንና በአቋማችን መግፋታችን ነው። የፈለጉት፤ በሉ፣ አሁን የዲሞክራሲ ጨዋታው አብቅቷል፣ በሰላም ቤታችሁ ግቡ፣ ከአምስት አመት በኋላም እንደዚሁ እንጫወታለን፣ ሲሉን፣ እሺ፣ እስከነበር ጊዜ ጨዋታው ቆንጆ ነበር፣ ብለን ፤

አመስግነን ወደ ቤታችን እንድንገባ ነበር:: ጨዋታውን ከምር መውሰዳችንን አልተረዱትም ነበር መሰል:: በመታሰር የሚገኝ ጀግንነት ወይንም ክብር አለ ብለን እራሳችንን ለዚያ መስዋእትነት ያለ ምክንያት የምናቀርብ ሞኞች ወይንም አጉል ብልጣ ብልጦች ሆነንም አይደለም:: ቢያንስ ብዙዎቻችን በእድሜ የገፋን፤ የቤተሰብ ሀላፊነት ያለብንና ይህንንም ሀላፊነታችንን የምንወጣ፤ የወጣትነት ግልፍተኝነት የሌለብን፤ አስበን የምንራመድ ደመ ቀዝቀዛ ሰዎች ነን:: ታዲያ ለምን የወሰነውን ውሳኔ ወሰንን? መልሱ በጣም ቀላል እና ብዙ ሊያስገርም የማይገባም ነው:: ምንም አማራጭ ስላጣን ነው:: ጊዜው ያቀረበልን ምርጫ የተነሳንበትን አላማ ፈጽሞ መርሳት ውይንም ማሽመድመድ፤ ወይም ለአላማችንና ለግባችን በጽናት ቆመን የውሳኔያችንን መዘዝ ጥሩም ሆነ መጥፎ በጸጋ መቀበል ነበር:: አላመችንን ሳንለቅ ግን ለተወሰነ ጊዜ (በግልጽ ለታወቀ) ለማሸጋገር እና ይህንንም በማድረግ አደጋውን ለመቀነስ ያለደረግነው ሙከራ የለም:: ኢህአዴግ የሰጠን ምርጫ ግን ዲሞክራሲንና ነጻነትን እንደ ጊዚያዊ ጨዋታ እድንረሳው፣ ይልቁንም የተፈቀደልንን ወንበር ይዘን፣ የተፈቀደው ጨዋታ አካል ሆነን፣ ሰላማዊ ኑሮአችንን እንድንኖር ነበር :: ይህ ግን ለእኛ ምርጫ አልነበረም :: ምርጫ 97 ይዞ የመጣውን የዲሞክራሲ መንፈስ እስከነአካቴው ደብዛውን ሊያጠፋ የሚችል ውሳኔ ከመወሰን ሌላኛውን ያነሰ አስከፊ ውጤት ያለውን ውሳኔ ወሰንን :: ስለዚህም እስር ገባን ::

ምን ውጤት አገኘን ? ይህን ጥያቄ በመጠኑም ቢሆን ለመመለስ የሚቻለው ከተነሳንበት አላማ እና የዚህን ውሳኔ ተጻራሪ አማራጭ ወስደን ቢሆን ኖሮ ሊከሰት ከሚችለው ውጤት ጋር በማነጻጸር ማየት ስንችል ብቻ ነው :: አላማችን ግልጽ እና ደጋግመን በይፋ የገለጽነው ነው:: በላንጣችንም እንዲሁ በግልጽ ከተናገርነው ውጭ የተደበቀ ሌላ አላማ ነበራቸው ብሎ ለማሳመን በፍርድ ቤት ያቀረበው ማስረጃ እራሱን ከማሳጣትና ፍ/ቤቱን በአለም ፊት ከቋስተቸት ውጭ ምንም ፋይዳ ያለው ነገር ስላላቀረበ በዚያ በኩል ብዙ አከራካሪ ጉዳይ ሊኖር አይችልም:: አላማችን በኢትዮጵያ እውነተኛ የዲሞክራሲያዊ ስርአት እንዲፈጠር ነው:: ይህንንም በሰላማዊ መንገድ ፤ የአገሪቱን ህጎች በመጠቀም ( የማናምንባቸውን ጨምሮ ) ፤ በነጻ ምርጫ ተወዳድሮ የሕዝቡን ድጋፍ ያገኘው ሀይል የፖለቲከ ስልጣኑን የሚረከብበት፤ የተለያዩ የመንግስት ተቋማት የሀገሪቱ የበላይ ህግ በሚያዘው መስረት ተግባራቸውን የሚያከናውኑበት፤ የመንግስት ስልጣን በህግ የተገደበበት፤ የዜጎች መብቶች የተከበረበት ሀገር እና የፖለቲከ ስርአት መመስረት ነው :: የኢትዮጵያ ሕዝብ መያዚያ 30 በሚሊዩኖች ወጥቶ በጨዋነት እቤቱ ሲገባ ይህን ስርአት ለማነጽ መፈለጉን ብቻ ሳይሆን በዚያ ስርአት ለመኖር መብቃቱን ነው ያሳየው:: ግንቦት 7 ቀን ከለሊቱ 10 ሰኣት ጀምሮ፣ በአንዳንድ ቦታዎች እስከ ሌሊት 8 ሰአት ድረስ ዝናብ፤ ብረድ፤ ፀሀይ፤ ሳይበግረው ቆሞ ድምጹን የሰጠው ከዴሞክራሲያዊ ስረአት ውጭ ለመኖር እንደማይሻ ለማሳየት ነው:: ከነጻ የሕዝብ ምርጫ ውጭ የሚመሰረት ማንኛውም አይነት መንግስት (በሌላም መስፈርት ምንም ያህል ጥሩ ቢመስልም፤ የተሻለ የልማት ውጤት ለማምጣት ችሎታና ብቃቱ ቢኖረውም ) ከአሁን በኋላ ምንም አይነት ተቀባይነት ወይንም ህጋዊነት ሊኖረው እንደማይቸል ነው ሕዝቡ በግንቦት 97 በግለጽ ያሳየው :: በጊዜውም ሆነ አሁን የቅንጅት እምነት ይኸው ነው:: የያኔ ውሳኔያችን እንግዲህ መመዘን ያለበት ከዚህ አጠቃለይ አላማ አንጻር ነው:: ከመታሰርና መታሰርን ከማምለጥ አኳያ ሊመዘን አይችልም:: በዚህ ስሌት ውሳኔያችንን ለመመልከት መሞከር አግባብ ያልሆነ ስለዚህም ፍሬ የማይሰጥ ድከም ብቻ ነው የሚሆነው :: ብቸኛ መለኪያው እኛ የቆምንለትና ህዝቡም ይገባኛል ብሎ የተቀበለውን ዴሞክራሲያዊ ስርአት ከመመስረት አኳያ ጠቅሟል ወይስ ጎድቷል ነው::

ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ደግሞ የአማራጩ መንገድ ውጤት ስለታዬ በጣም ከባድ ሊሆን አይገባም። እኛ የወሰነው ውሳኔ (በተለይም ያቀረብናቸው ባለ ስምንት ነጥብ ጥያቄዎች ምንነት)፤ ይህ ያስከተለው የኢህአዴግ እርምጃ፤ ለኢህአደግ እርምጃ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የሚገኙ ኢትዬጵያውያን ያደረጉት እንቅስቃሴ፤ የአለም ሕዝብ በአቶ መለስ መንግስት ላይ ያኔ የነበረውን አመለካከት አሁን በያዘው ግንዛቤ እንዲቀይር አድርጎታል። የኢህአዴግ ፓርላማ፤ ፍርድ ቤቶች፤ የፖሊስና የደህንነት አካላትና ሌሎች የመንግስት ተቋማት ባለፈው ሁለት አመት የሰሩትን ስራ በመመዘን (እኛ ፓርላማ ገብተን ቢሆን ኖሮ ይህ ነበርና የሚቀጥለው ወይንም ደግሞ በዚህ ሁኔታ እንዳይቀጥል ያቀረብነውን ጥያቄ አሌ ብሎ ነውና እርምጃውን የወሰደው ) ለእውነተኛ የዲሞክራሲ ስርአት የትኛው አንድ ኢንች ወደፊት ገፍቶናል የሚለውን ቀላል ጥያቄ በመመለስ እናገኘዋለን። በእኔ እምነት የአቶ መለስ መንግስት የወሰደው እርምጃ የሄደበት መንገድ በዲሞክራሲው ስርአት ግንባታ ሂደት ሀገሪቱን ወደኋላ የጎተተ ቢመስልም፤ በወሰደው እርምጃ የእራሱን ማንነትና ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ፍጹም ብቃት የሌለው መሆኑን ከመሳየት ውጭ፤ ከእዚህ በፊት ተደብቆ ይኖርበት የነበረውን የማስመሰያ ሂደት እርቃኑን ከማውጣቱ በቀር፤ እኛ ፓርላማ ገብተን ቢሆን ኢህአዴግ የሚያመጣው የተለየ ነገር አይኖርም ነበር። ዴሞክራሲ የሚጠይቀውን የተገደበ ስልጣን ለመቀበል ቅንጣት እንኳን ፍላጎት ቢኖረው ኖሮ እኛ ያቀረብነውን ጥያቄ ይቀበል ነበር። ቢያንስ ለመደራደር እንኳን ፈቃደኛ ይሆን ነበር። ስለዚህ በአማራጩ መንገድ ባለመሄዳችን የታጣ ነገር የለም። ይልቅስ የተወሰኑ ጥቅሞች ነበሩት።

የመጀመሪያውና ትልቅ ጥቅም የኢትዮጵያ ሕዝብ ፓለቲካን የጥቂት አፈጮሌዎች፣ የማን ይበልጥ የወሬ ፉክክር አድርጎ እንዳያየውና ዴሞክራሲያዊ ፓለቲካ የወሬ ሳይሆን የተግባር ፓለቲካ እንደሆነ በደንብ እንዲረዳ አድርጎታል ብዬ አምናለሁ። በዚህም ምክንያት ከአሁን በኋላ የፓለቲካ ሀይሎች የሚለኩት ሕዝቡ በግንቦት 97 ላሳየውና ሙሉ ለሙሉ ለቆመለት የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ በቁርጠኝነትና በተግባር መቆም አለመቆማቸው ሆኖአል የሚል ግምት አለኝ። ይህ ደግሞ የረጅም ጊዜ ጥቅም ነው።

ሁለተኛ፤ ዴሞክራሲያዊ ሥርአትን የሚፈልጉት ጥቂት ተመሳሳይ (ለምሳሌ በባህል ስብስብ መስፈርት) ሰዎች ሳይሆኑ ሁሉም ፍትህ ፈላጊ ኢትዮጵያዊ መሆኑንና ይህንን ስርአት በዘርና በሃይማኖት ወይንም ሌላ ብሄረተኛ ርዕዬተ አለም የሚተካው አለመሆኑን ያሳየ ይመስለኛል። በዚህም ምክንያት በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያውያን መካከል የተሻለ የአላማ መቀራረብ የተፈጠረ ይመስለኛል። ይህም ለዘላቂ የዲሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ወሳኝ ነው።

ሶስተኛና እጅግ ጠቃሚና አስፈላጊው ውጤት ምናልባትም ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያችን መሠረተ ሰፊ የሆነ እውነተኛ የዲሞክራሲ (mass movement for democracy) ተፈጥሮል። እስከ ዛሬ ከዳር ቆመው የነበሩ፤ ለፓለቲካ ጉዳይ ቁብ የማይሰጡ በጣም ብዙ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች፤ ጎልማሶችና ኮረዶች፤ የተማሩና ያልተማሩ፤ ከተሜዎችና ባላገሩ ስሜቱን የገለፅበት መንገድና ለትግሉ ያለውን አጋርነት ያሳየበት መንገድ ምንም ያህል የተለያየ ቢሆን ዘርና ሃይማኖት ሳይለይ ለፍትህና ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ያለውን ወገንተኛነት ያሳየበት ጊዜ ነው።

በመጨረሻም ይህ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በግልጽ ያበሰረው ነገር አለ። ይኸውም ከዚህ ቀጥሎ በኢትዬጵያችን የሚፈጠረው መንግስት ምንጩ ምንም ይሁን ምን ዲሞክራሲያዊ ከመሆን በቀር ምንም

አማራጭ የሌለው መሆኑን ነው:: በመለያዬት ፖለቲካ ማህበረሰባችንን ከአሁን በኋላ ከዲሞክራሲ ማራቅ አይቻልም :: የከዚህ በፊት በደልና ጥቃት የዛሬንና የነገን ኢ-ፍህታዊነት ለመሸፈኛ ሊውል አይችልም:: ሌሎች ችግሮቻችንን ለመፍታት (ለምሳሌ ድህነትን) ዛሬ ኢዲሞክራሲያዊነትን መቀበል ይገባናል የሚል አካሄድ ከአሁን በኋላ በኢትዩጵያችን ተቀባይነት አይኖረውም:: በአጠቃላይ ያለፈው ሁለት አመት ኢትዩጲያዊያንን በመንፈስ ሊዲሞክራሲ አዘጋጅቷቸዋል:: ይህ ቀላል ውጤት አይደለም:: ለዚህ የተከፈለ መስዋአትነት የሚያም ቢሆንም በምንም አይነት መና የቀረ መስዋእትነት አይደለም:: ዲሞክራሲን እውን ለማድረግ መከፈል ያለበት ወይም የነበረበት ነው:: ለዚህም ነው በዚህ ትግል ውስጥ ለተሰውት የዲሞክራሲ ሰማእታት ከፍተኛ ክብር ያለንና ምን ጊዜም የማንረሳቸው::

ለዲሞክራሲያዊ ስርአት መመስረት መንገዱ ተጠረጓል :: አሁን የቀረው መንገዱ ላይ ያሉትን አባጣ ጎርባጦች ማነሳሳትና ከእየቦታው የተሰባሰቡ ቆሻሾችን መጠራረግ ብቻ ነው:: ይህ ግን ቀላል ነገር አይደለም:: ብዙ ሥራ ይጠይቃል :: ብዙ ስልታዊ ማሰብን ይጠይቃል :: በመንገዱ ላይ የተደቀነ በቀላሉ መሸፈን የሚችል ጎድጓዳ ቦታ መኪና ለመገልበጥ እና አደጋ ለማስከተል የሚቻለውን ያክል፤ ለዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ በምናደርገው ጉዞ በመንገድ ላይ የሚገጥሙንን እንከኖች በብልሀት፤ በስልት፤ በመቻቻል፤ በሰጥቶ መቀበል ባጠቃላይ ይህ ስርአት በረጂም ጊዜ ሂደቱ ያከበታቸውን የሂደት ልምዶች በመጠቀም መፍታት ይኖርብናል:: ለዚህም ነው ከአሁን በኋላ ብዙ ጊዚያችንን ወደምንፈልገው ስርአት ስንሄድ የሚገጥሙንን ችግሮች ሰለምንፈታበት መንገድ መወያዬት አለብን የምለው:: እኔም በዚሁ ወደእዚያ ጉዳይ ልለፍ ፤

### 3. የትላንትናውን ከመቆፈር የወደፊቱን በጥራት ማየት ፤

ባለፈው ሳይሆን በወደፊቱ ላይ ማተኮር አለብን ስንል ያለፈውን ፍጽሙኑ መርሳታ አለብን ለማለት አይደለም :: እንዲያውም ከምንም ነገር በላይ ካለፈው መቅሰም ያለብንን ትምህርቶች በጥራት ማስቀመጥ ፤በማያወላዳ መንገድ ወደፊት የሚያስኬደንን ተግባራዊ ግንዛቤ መጨበጥ ለወደፊት መንገዳችን ትልቁ ስንቃችን ነው የሚሆነው:: ከታሪክ ያልተማሩ የታሪክን ስህተት ይደግማሉ እንዲሉ፤ ስለወደፊቱ ስናስብ ትልቅ ጥንቃቄ ማድረግ ያለብን በታሪካችን የተሰሩ ስህተቶችን ( የስህተቱ ምንጭ ማን ሆነ ማን ) እንዳንደግም ነው :: ሰለዚህም ለዚህ ውይይታችን ጥሩ መነሻ የሚሆነው ከአለፈው የተማርነውን በግለጽ ማስቀመጥ ነው:: በእኔ እምነት ይህ የአጭር ጊዜ ልምድ ያለው አኩሪ የዲሞክራሲ ትግላችን ውጤታማ ሆኖ ወደ ግባችን እንዲያደረሰን ከአለፈው መማር ያለብን ቢያስነስ የሚከተሉት ትምህርቶች አሉ ::

**3.1** በመጀመሪያ በትግላችንና በግባችን ላይ ግልጽ የሆነና ምንም ብዥታ የሌለው አመለካከት ሊኖረን ይገባል:: ግባችን በፍትህ ላይ የተመሰረተ የፖለቲከ ማሕበረሰብ መፍጠር፤ የዚህ አይነት ስርአት ብቸኛ ው መንገድ ደግም ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርአት መሆኑን ያለምንም ማመንታት ወይንም ብዥታ መቀበል ነው:: ከዚህ ውጭ በማሕበረሰባችን ላይ ሊጫን የሚፈለግ ምንም አይነት መሠረታዊ እምነት (fundamental principle)፤ በሌሎቹ መስፈርት ምንም ያህል ሊያማልል የሚችል ቢሆንም ተቀባይነት ለኖረው አይገባም:: ምንም ጊዜ መርሳት የሌለብን ያለንና ወደፊትም የሚኖረን የፖለቲከ ማሕበረሰብ በመሰረታዊ የኑሮ እምነቶች ላይ በጣም የተለያየና በዚያ ደረጃ ልናቀራርበው የምንችለው አለመሆኑን ነው:: ለምሳሌ እምነትን በመሰለ ግዙፍ ጉዳይ ላይ ማህበረሰባችን የተለያዩና ሁሉም የራሳቸውን

እምነት አጥብቀው በሚያምኑ የባህልና የሀይማኖት ስብስቦች የተከፋፈለ ነው ። የምንፈጥረው የፖለቲካ ማሕበረሰብ ይህንን ልዩነት የተቀበለ ብቻ ሳይሆን ሁሉም የራሱን ይዞ በሰላም ሊኖር የሚችልበትን መንገድ የሚያመቻች ነው። የጋራ የፖለቲካ ሕይወታችንንም በተመለከተም አንድ አይነት አመለካከት እንዲኖረን አይደለም የሚጠበቅብን። እንዲያውም ልዩነቶች በመሃከላችን መኖራቸው ነው የሚጠበቀው። መስማማት ያለብን ልዩነቶቻችንን የምንፈታበት ስልት ላይ ነው። ይኸውም የፖለቲከ ስልጣን ምንጭ በነጻ ምርጫ የሚገኝ የሕዝብ ድምጽ በመሆኑ ላይ መስማማት ብቻ ነው። በዚህ ላይ ፀብ ከሌለ ለጋራ የፖለቲካ ህይወታችን ልንቀበላቸው የሚገቡን መሠረታዊ የእኩልነት መርሆዎች ሁለት ብቻ ናቸው። እነኝህም፤ በፖለቲካ መስክ ሁሉም ዜጋ እኩል ድምጽ አለው የሚለውና የፍትህ መሰረት የሆነው ሁሉም ዜጋ በህግ ፊት እኩል ነው የሚሉት ሁለት መርሆዎች ናቸው።

**3.2** ሁለተኛውና አስፈላጊ የሚመስለኝ ትምህርት በዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ሂደት ያለንበትን ደረጃ በቅጡ ለየቶ ማየትን አስፈላጊነት ይመስለኛል። ዴሞክራሲያዊ ስርአትን በአንድ አገር ለመጀመሪያ ጊዜ ለመትከል የሚደረግ ትግልና ዴሞክራሲያዊ ስርአት ተተክሎ በማያወላዳ ሁኔታ በሁለት እግሩ በቆመበት አገር ውስጥ የሚደረግ የፓለቲካ ትግልን ለይተን መገንዘብ ከብዙ አላስፈላጊ ግጭቶች ያድነናል የሚል እምነት አለኝ። ይህንን ስርአት በመጀመሪያ ጊዜ ለመትከል በሚደረግ የትግል ሂደት ውስጥ ብዙ ጥቅሞችና ፍላጎቶችን አቻችሎ መጉዋዝ ለስርአቱ ግንባታ አስፈላጊ በመሆኑ የበለጠ ትእግስትን፤ የአመለከከት ለዘብተኝነትን፤ የማቻቻል ችሎታን ይጠይቅብናል። ማንኛውም አይነት አከራሪ አመለካከት የሚሰጠው የፍፁም ትክክለኛነት ስሜት ስርአቱን ለመገንባት በሚደረግ ሂደት እንቅፋት ሊሆን ይችላል። ሥርአቱ ከተመሰረተ በኋላና የሕዝብ ወሳኝነት ጥያቄ ውስጥ በማይገባበት ወይንም የስርአቱ ተቋማት ነፃነታቸውን አስጠብቀውና ተደላድለው በሚሰሩበት ሁኔታ ያሉንን የፓለቲከ አመለከከቶች አክርረን ብንይዛቸውና ከነሙሉ ስሜታችን ብንገባባቸውም በዚያ ምክንያት የሚፈጠሩ ግጭቶች ሥርአቱን ለአደጋ አይጥሉትም። ስለሆነም በዜጎች መሀከል ያሉ ልዩነቶችን በፍትሃዊና በፓለቲካ እኩልነት መርህ መሠረት ለመፍታት የሚችሉ ተቋማት ባሉበት በትናንሽ ጉዳዬች ጠንካራና የከረረ አቋም መያዝ ትክክል እንኳን ባይሆን አደጋው የከፉ አይሆንም። ለዋናው ዲሞክራሲያዊ ስርአት በሚታገሉ አገሮች ከችግራቸው አኳያ ሲታይ ጥቃቅን የሚመስሉና የሆኑ ጥያቄዎች የበሰለ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ባለበት ዜጎች በከፍተኛ ስሜታዊነት ሲከራከሩበት የምናየውና የክርክሩ ጠንካራነት የሚገርመንም የእኛን ችግር ግዝፈት ከነሱ ልዮነቶች ትንሽነት በትክክለኛው መለኪያ ላይ አስቀምጠን ስለማናየው ነው። እነሱ ብዙውን የማቻቻልና የትዕግስት ስራ ወሳኝ በሆነው የሥርአቱ ግንባታ ጊዜ በብልህነት ተወጥተውታል። እኛ አሁን ያለነው እነሱ ከምእተ አመታት በፊት የነበሩበት ደረጃ ላይ ነው። ለዚህ ነው ለዴሞክራሲያዊ ሥርአት ግንባታ በሚታገሉ ሀይሎች መሀከል ያለውን ልዩነት ሳናገዝፍ ሥርአቱን በሁለት እግሩ እስከምናቆመው ድረስ በከፍተኛ ትዕግስትና ብልህነት መጎዝ አለብን የምለው። ችግሮቻችንን በሰላም የመፍቻውን ሥርአትና ተቋማት በተገቢ ቦታቸው ካኖርን በኋላ ባሉን ልዮነቶች ላይ በአስፈላጊው ስሜት (PASSION) በኋላ እንመለስባቸዋለን። እስከዚያው የእርስ በእርስ መጎነታተላችንን፣ ትንሽ ከስሜታዊነት ልንገድበው እንደሚገባ አለበለዚያ ግን ውስጣችን በሚኖር ክፍፍል አላማችንን ስተን የፅረ ዴሞክራሲ ሀይሎች ሰለባ እንዳንሆን መጠንቀቅ እንዳለብን የዚህ ያለፈው ሁለት አመት ታሪካችን በቂ ትምህርት ሰጥቶን አልፏል ብዬ እገምታለሁ።

**3.3** ሌላው የቅርብ ታሪካችን ትምህርት የያዝነውን አላማ ለማሳካት የሚጠይቅብንን መሰዋዕትነት በቅጡ መረዳት ነው። በአገራችን እውነተኛ ዴሞክራሲ እንዲመሰረት የማይፈልጉ ሀይሎች ይህን ስርአት እንደጦር የሚፈሩበት ግልፅ ምክንያት አላቸው። በችሎታቸው፤ በብቃታቸው ወይንም ከሚፈጥሩት ውጤት ጋር ባልተገናኘ የሚያገኙት (የማቴሪያልም ሆነ የስልጣን) ጥቅም አላቸውና ያንን ጥቅማቸውን ላለማጣት (እራሳቸውን ለመሸንገያ የሚሰጡትን መርህ ነክ ምክንያቶች ከቁም ነገር ሳንቆጥር) የተቻለውን ያክል መታገላቸው የማይቀር ነው። እውነተኛ ዴሞክራሲ ባለበት፤ ነፃ ምርጫ በሚካሄድበት ሁኔታ በቀላሉ ሊሸነፉ እንደሚችሉ የግንቦቱ ምርጫ ከተዘፈቁበት የራስ ማታለል ጥልቅ ቅዥት ውስጥ በድንገት አባንኖ አሳይቷቸዋል። ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ለመቅጠፍ፤ ለማጭበርበር፤ ለማሰር፤ ለመግደል የማይመለሱ፤ እራሳችንን ዝቅ ያደርጋል ብለው በማሰብ ከመተግበር ወደ ኋላ የሚሉት ምንም ስልት እንደሌለ አሳይተዋል። በዴሞክራሲ ስም ምለው የሚገዙት የውጭ ሀይሎችም ከምንም ነገር ባለይ ጥቅማቸውን እንደሚያስቀድሙና የዴሞክራሲ ስርአት በሕዝብ ሀይል እስከሚፀድቅ ድረስ ለዴሞክራሲ በሚታገለው ሕዝብ ላይ የሚፈፅመው በደል ብዙም እንቅልፍ እንደማይነሳቸው አሳይተውናል። ስለዚህ ዲሞክራሲያዊ ስርአት በሃገራችን እንዲመሰረት የምንፈልግ ከሆነ ከማንም በስጦታ የምናገኘው ሳይሆን በራሳችን ትግል የምናገኘው መሆኑን ጠንቅቀን መረዳት ይኖርብናል። ይህን ከተረዳን ትግሉ ውስጥ የምንገባው ሊያስከፍለን የሚችለውን መሰዋትነት አውቀንና ተረድተን ለሱም ተዘጋጅተን ስለሚሆን  እዳውን ለመሸከም አይከብደንም፤ በቀላሉም ተስፋ አንቆርጥም። እነሱ የማይገባቸው ስልጣን ላይ ለመቆየት በጉልበት የያዙትን ስልጣንና ከሕዝቡ ያለአግባብ የሰበሰቡትን የሕዝብ ንብረት በመጠቀም የሚያሳርፉትን ጫን ለመቋቋም የሚችልና አልፎም ለማሸነፍ የሚያስችል እልህና ቁርጠኝነት ሊኖረንና ልናዳብረው የምንችለው፤ ትግሉ የሚጠይቀንን እዳ ልክ ስናውቀውና ለሱም በበቂ ስንዘጋጅ ነው። የዚህን እዳ ልክ ደግሞ ባለፈው ሁለት አመት በደንብ የተገነዘብነው ይመስለኛል። እዳው ከፍተኛ ነው ። ግን ልንቋቋመው ከምንችለው በላይ ከቶም አይደለም።

**3.4** ሌላው ከቅርብ ታሪከችን መቅሰም ያለብንና ፈፅሞ መዘንጋት የሌለብን ትምህርት አሁን ካለንበት ቦታ በትግል ሂደት የምንደርስበት ግባችን ብለን የምናስበው የዴሞክራሲያዊ ሥርአት ቅርጹም ሆነ ይዘቱ በትግሉ ሂደት የሚወሰን መሆኑ ነው። ዴሞክራሲያዊ ሥርአት ስልጣን ከተያዘ በኋላ የሚመጣ፤ የአሁኑ ጊዜ አትኩሮታችን አሁን ያለውን ኢፍትሀዊ ስርአት በመታገል ላይ ብቻ ማተኮር እንዳለበት፤ በዚህ ሂደት ውስጥ የምንከተለው ስልት፤ የምንጠቀምበት መሳሪያ በኋላ ከምንፈጥረው ስርአት ጋር ምንም ያልተያያዘ እንደሆነ አድርጎ ማሰብ በእርግጥም ታሪካዊ ስህተትን መድገም ነው። በትግሉ ሂደት ፍትሀዊነትን መመሪያችን ከላደረግን፤ ወደ ግባችን የሚወስደን መሳሪያ አድርገን የምንጠቀምበት የፓለቲክ ድርጅት ከአወቃቀሩ ጀምሮ እስከ መሪዎቹን የሚመርጥበት መንገድ ፍፁም ዴሞክራሲያዊ ከልሆነና የገዛ አባላቱን ለእንዲህ አይነት  ውስጠ ድርጅት ዴሞክራሲ ብቁ አይደለም ብሎ ከገመተ፤ ወይንም እንቅስቃሴው ውስጥ በተለያየ የሃላፊነት ቦታ የሚመደቡ አባሎቹ ለስራው ባላቸው ብቃት ከልተመደቡና ብቃታቸውን መወጣት ከልቻሉ ከሃላፊነት መነሳት የሚችሉበት ተጠያቂነትን መሠረት ያደረገ የውስጥ አሰራር በትግሉ ሂደት ውስጥ ካልመሰረትን፤ እነኝህን መርሆዎች መሠረት ያደረገ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ሥልጣን ከያዝን በኂላ በአገሪቱ ላይ እንመሰርታለን ማለት ፍፁም ዘበት ነው የሚሆነው። ያልዘሩትን አያጭዱም እንደሚባለው፤ በትግላችን አሸንፈን የሚመሰረተው ሥርአት በአብዛኛው በትግሉ ወቅት የነበረንን መልክ ነው የሚያሳየን። ስለዚህ ይህ ለዴሞክራሲ ሥርአት ግንባታ የተነሳሳ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ከአሁኑ ጀምሮ ያንን ሥርአት ለማምጣት ብቃት ባለው ዴሞክራሲያዊ አደረጃጀት መገንባት አለበት። ይህንን በአንድ

ቀን ማድረግ አንችል ይሆናል፡፡ ወይንም ደግሞ በትግሉ ሂደት በዚህ ዙሪያ ምንም ስህተት አንፈጽምም ማለትም አይደለም፡፡ ወይም አንዴ ስህተት ከፈፀምን ተስፋ የለውም ብለን እንደ ቦክሰኛ ፎጣውን ወርውረን፣ ተስፋ ቆርጠን እቤታችን እንገባለን ማለት አይደለም፡፡ ከዚህ አኳያ ዋናው አላማ መሆን ያለበት በመርህ ደረጃ ዴሞክራሲያዊ አደረጃጀትን መቀበል፤ በተለያየ ምክንያት በዚህ መልክ ያልተደራጅ የድርጅቱ አባሎች ካሉ በሂደት ዴሞክራሲያዊ ቅርፅ በቶሎ እንዲያዙ ማድረግ፤ አዲስ የሚቋቋሙ አካሎችን በዚያ መልክ ማደራጀትና ስህተቶችን በቶሎ ማረም የሚያስችል ክፍትና እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ባህል በእንቅስቃሴው ውስጥ እንዲሰፍን አጥብቀን መጣር ነው፡፡ ይህንን ማድረግ ስንችል ብቻ ነው ግንቦት 97 በሕዝባችን ዘንድ ለተፈጠረው ትልቅ የዴሞክራሲ መንፈስ ብቁ ሆነን መገኘት የምንችለው፡፡ ለዚህ ደግሞ ብቁ ሳንሆን የዴሞክራሲ እንቅስቃሴውን ከቶውንም ልንመራው ቀረቶ ተከታዩ እንኳን ልንሆን አይቻለንም፡፡

**3.5** ከዚህ ጋር የተያያዘ ልንመሰርት የምናስበው ሥርአት እንደ ድርጅትና እንደ እንቅስቃሴ ብቻ ሳይሆን እንደ ግለሰብ ዜጎች የሚጠይቀን ለዚያ ስርአት ብቁ የሚያደርገን ባህርይ አለ፡፡ የዚህ ባህርይ በስፋት አለመኖር ወይንም እንዲኖር ማስፈለጉ አንዱ ከታሪካችን ልንቀስም የሚያስፈልገን ትልቅ ትምህርት ይመስለኛል፡፡ ምንም እንኳን ዴሞክራሲያዊ ሥርአት በጥልቀት ተመስርቶባቸዋል በሚባሉት አገሮችም የዚህ ባህርይ እጥረት በፓለቲከኞቻቸው ዘንድ በስፋት ሲከሰት ቢታይም እኛ ጋ እንደሚታየው በፍፁም ለከት ባጣ ደረጃ ባለበት ሁኔታ ዴሞክራሲያዊ ስርአት መመስረት እጅግ አዳጋች ነው፡፡ ዴሞክራሲያዊ ፓለቲካ በመሰረቱ የጨዋ ፓለቲካ ነው፡፡ በግለሰብ ደረጃ ለሰው ልጅ ከፍተኛ ክብር አለው፡፡ አንዳንዴ በሂደት ሊያጋጥም ቢችልም እንደ ግብ ይዞ የሚነሳው በተቻለ መጠን በእውነት ላይ የተመሰረተ ክርክር፤ አይን ካወጣ ውሸትና ቅጥፈት እራስን ማፅዳት፤ ለባላንጣ አመለከከት ተገቢውን ክብር መስጠት (በተቻለ መጠን የባላንጣችንን ጠንከራ መከራከሪያ ወስደን እሱን በአምክህኖትና በጭብጥ እውነቶች ላይ በተመሰረተ መዋጋት)፤ በተገቢው ሳያጣሩ ባልተረጋገጡ ወሬዎች ላይ በመመስረት የራስን አመለካከት ከመቅረፅ መቆጠብ፤ ከሴትዬዋ/ሰውየው ማንነት ይልቅ በሚቀርበው መከራከሪያ ላይ ማተኮር፤ የሰውን ስብዕና ጥላሸት ለመቀባት አለመቻኮል፤ ለዴሞክራሲ ተቋማት አክብሮት መኖር ወዘተ. የመሳሰሉት ባህርያት ለዴሞክራሲያዊ ሥርአት ማበብ አስፈላጊ የሆነ የፓለቲካ ውይይትና ትግል ባህርያት ናቸው፡፡ የፓሊቲካ ውይይት ባህላችን ይህ ጨዋነት ከጎደለው በእንቅስቃሴው ውስጥ ሊገቡ የሚችሉና የሚፈልጉ፤ ለእንቅስቃሴው የሚጠቅም ብዙ የግል ችሎታ ያላቸው ሰዎች ትግሉን እንዲሸሹ አልፎም ፓለቲካ የሚባል ነገርን እንዲጠሉ ያደርጋቸዋል፡፡ ትግሉንም ጠንካራ ሊሆኑ የሚችሉ መሪዎች ያሳጣዋል፡፡ እጅግ ሲከርርም በፓለቲካው መስክ የሚሰማሩት ሰዎችም ይህንን ጤንነት የጎደለው የፓሊቲካ ሽኩቻ መመከት የሚችል ጠንከራ ቆዳ ያላቸው ሰዎች ብቻ የሚሰባሰቡበት (ምናልባትም ከሌላ ብቃት ይልቅ ይህ ችሎታ ትልቅ የብቃት መለኪያ የሚሆንበት) አልፎም እነሱ ራሳቸው በዚህ የብልግና ፓለቲካ የተካኑ ብቻ ይሆኑና የፓለቲካ ስርአቱን ይዘት ብቻ ሳይሆን መልኩንም ያበላሹታል፡፡ ይህ በኢትዮጵያ የፓለቲከ ባህል ስር የሰደደ በሽታ ከዚህ በፊትም የነበረና ኢዲሞክራሲያዊ ስርአት የመመስረት ተጋድሎ ቅሪት ነው የምንልም ከሆነ አሁን በአዲስ ደረጃ እንመሰርታለን ከምንለው እውነተኛ የዴሞክራሲ መንፈስ ጋር ፈፅሞ የማይሄድ ስለሆነ ሁላችንም ይህን አስቀያሚ መልኩን በሚያሳይበት ቦታ ሁሉ በቶሎ ልንከረኩመው ይገባል፡፡ በዚህ ዙሪያ በተለይ አመለካከታችንን በሀሳባቸው ከሚቀርፁት ምሁሮቻችን ዘንድ በሰፊው የሚጠበቅ ትግል ነው፡፡ በዴሞክራሲያዊ ክርክር በጥሩ መከራከሪያ ባላንጣውን ማሳመን ወይም ማሸነፍ ያቃተው ደከማ ሰው ብቻ ነው፤ ስም ማጥፋትና የሀሰት ወሬን እንደ መከራከርያ ስልት ለመጠቀም

ፈቃደኛ የሚሆነው:: እንዲህ አይነት ዝንባሌ ያለው ሰው ደግሞ የፖለቲካ ስልጣን አከባቢ ሲገኝ በፖለቲካ ክርክር ያሸነፈውን ወይንም የልቻለውን ሰው በጉልበቱ አፉን ለማዘጋት ወደኋላ እንደማይመለስ መገመት ሊያቅተን አይገባም:: በዚህ መልክ አሁን በፖለቲከ ባላንጣዎች ላይ የሚታይ የአፍ ጨካኝነት ነገ ወደ አፈና እንደሚሸጋገር እንደሁኔታውም የዛሬ የወገን ሀይሎች በባላንጣ ላይ ሲደረግ ዝም ብለው ካዩ ነገ በሚቀየረው ፖለቲካ ዛሬ ወገን የነበረው ነገ ባላንጣ ሆኖ በሱም ላይ ሊደርስ እንደሚችል በመገንዘብ ሌላ ቢቀር ነግ በኔ ነውና ከአሁኑ ይህ ባህሪይ በጣም ስር ሳይሰድ አጥብቀን መታገል እንዳለብን ለማስገንዘብ ያህል ነው ::

**3.6** በመጨረሻ በፍጹም ልንረሳው የማይገባን የሚመስለኝ ትምህርት ዴሞክራሲያዊ ሥርአትን የመገንባት ትግል በተናጠል በአንድ ድርጅት ወይንም ጥቂት ስብስቦች የሚደረግ ትግል ሳይሆን በብዙ ሰዎችና ድርጅቶች የጋራ ትግል የሚገኝ ፍሬ መሆኑን ከልምዳችን የተገነዘብነው ይመስለኛል:: ለዲሞክራሲ የሚደረግ ትግል ጠላቶቹን እየቀነሰ ወዳጆቹን እያበዛ መሄድ ያለበት ትግል ነው:: በአንድ ምክንያት ወይንም በሌላ መብታቸው የተረገጠ ሀይሎች፤ የኢፍታዊነት ሰለባ የሆኑ ስብስቦች፤ በመሰረታዊ ጥያቄዎች ላይ ያላቸው አመለከከትና እምነት ምንም ሆነ ምን በመጨረሻው የፖለቲካ እምነታቸውን በሕዝብ ድምጽ ለማስገዛት (እመነታቸውን ግን እንደያዙና ወደፊት እንደገና የሕዝብ ድጋፍ ለማግኘት የሚያደርጉትን ጥረት በማወቅ) አስከወሰኑ ድረስ የዚህ ሰፊ ሕዝባዊ ትግል አካል የማይሆኑበት ምንም ምክንያት የለም:: እንዲህ አይነት ሰፊ ሕዝባዊ ትግል ለማካሄድ የሚሰባሰቡት ሀይሎች የግድ መስማማት ያለባቸው ከላይ በጠቀስኳቸው ሁለት የፖለቲካ መርሆች ላይ ብቻ ነው :: እነኝህም የፍትሀዊ ስርአት መሰረት የሆነውና የህግ ልእልና ትርጉም እንዲኖረው አስፈላጊ የሆነው ሁሉም ዜጎች በህግ ፊት እኩል የመሆናቸውን መርህ መቀበል አንደኛው ሲሆን ፤ ሁለተኛውና ከዚህም መርህ ግር በጥብቅ የተገናኘው የፖለቲካ ልዩነትን በሕዝብ ድምጽ ለመፍታት የሚያስችለው የሁሉንም ዜጋ የፖለቲካ እኩልነት መቀበል ናቸው:: እነኝህን ከልቡ የተቀበለ ግለሰብ ወይንም የፖለቲካ ስብስብ እራሱን በዴሞክራሲያዊ ስርአት ለማስገዛት የወሰነ ነውና የዴሞክራሲዊ ትግሉ አካል የማይሆንበት ምንም ምክንያት የለም:: መሆን ይችላል ብቻ ሳይሆን እንዲሆን መደረግ ያለበት ጥረት ሁሉ መደረግ አለበት:: የፖለቲካ እምነቱን በሕዝብ ድምጽ ለመፈተን የፈቀደ ሀይል ይህንን የዴሞክራሲ እንቅስቃሴ ለመቀላቀል ሊያግደው የሚችል ብቸኛ እንቅፋት ሊሆን የሚችለው እነኝህን በትግሉ ወቅት የሚሰባሰቡ ሀይሎች የጋራ ትግላቸው በዲሞክራሲ አሸናፊነት ተጠናቆ የፖለቲካ እምነታቸውን ሕዝብ ፊት አቅርበው የሕዝብ ፍርድ እስኪያገኙ ባለው የትግል ጊዜ የሚኖራቸው የሀላፊነት ሚና በምን ይወሰናል የሚለው ነው:: በቀላልና በቀጥተኛ አነጋገር በትግሉ ወቅት የሚሰባሰቡት ድርጅቶችና ግለሰቦች በመሀከላቸው የሚኖረውን የአመራር ሀላፊነት እንዴት ይከፋፈሉታል የሚለው ጥያቄ ብቻ ነው:: ይህ በርግጥም ቀላል ጥያቄ አይደለም:: ትግሉ ፍሬ እዲያፈራ በአመርቂ ሁኔታ መመለስ አለበት:: ግን ከላይ የጠቀስኩትን መለመድ ያለበት የውይይት ባህል ከምር ከወሰድነው፤ ለዴሞክራሲ ሥርአት ግንባታ የሚደረገው ሰፊ አገራዊ እንቅስቃሴ እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ አደረጃጀትና አሰራር ሊኖረው እንደሚገባ ከተስማማን፤ ይህንን የሀላፊነት ድልድል ፍትሀዊና ሁሉንም ሙሉ በሙሉ ባያስደስት እንኳን ሊያግባባ በሚችል መልኩ ለመፍታት ይቻላል የሚል እምነት አለኝ :: ዋናውና በኋላ የፖለቲካ አላማን በተግባር ለመመንዘር የሚያስፈልገውን እውነተኛውን የፖለቲካ ስልጣን በሕዝብ ፊት በነጻ ተወዳድሮ ለማሸነፍ የተዘጋጀ ሀይል፣ ከብዙ ድከምና ልፋት በስተቀር በግል የሚገኝ ምንም የቁሳቁስ ሆነ የስልጣን ጥቅም በማይኖረው በትግሉ ሂደት ወቅት በሚሰጥ ሃላፊነት ምክንያት በሚደረግ ሹኩቻ፣ የጋራ ትግሉ ፍሬ እንዳያፈራ እንቅፋት መሆን ሌላ ቢቀር አምክኖታዊ ከሆነ የግል ጥቅም ( rational

self interest ) ጋር ብዙ አይጣጣምም ። በሌላ በኩል ግን በጋራ አለመታገል ሊያመጣ የሚችለውን ጉዳት፤ ለኢዲሞክራሲያዊ ሀይሎች የሚሰጠው የሞራልም ሆነ ሌላ ጉልበት ባለፈው ሁለት አመት እንኳን ያየነው ነውና ይህን ትምህርት አሁን በቅጡ ካልቀሰምነውና በቶሎም በተግባር ከላዋልነው ሌላ ሳይሆን የራስን ጥቅም እንኳን በቅጡ አለመገንዘብን ስለሚያሳይ ጅልነት ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው ። በስልጣን ላይ ያለው ኢዲሞክራሰያዊ ሀይል ዲሞክራሲያዊ ሀይሎችን ለመከፋፈል ሌት ተቀን የሚሰራውና ከፍተኛ የሕዝብ ንብረት የሚያጠፋው፤ የበግ ለምድ የለበሱ ተኩላዎችን በዲሞክራሲ ትግሉ ውስጥ አስገብቶ ከስር ለመቦርቦር የሚሞክረው፤ ዴሞክራሲያዊ ሀይሎች ትግላቸውን ካስተባበሩ የእሱ እድሜ ፍጽም እንደሚያጥር በቅጡ ስለሚገነዘበው ነው። ለዚህም ነው እኛም በዲሞክራሲያዊ ትግሉ ክልል ስር የምንገኝ ሀይሎች ሁሉ ተባብረን ተከባብረን፤ የአንዳችንን ድክመት በሌላችን ጥንካሬ እየሸፈንን፤ ተጋግዘን ኢፍትሀዊና ኢዲሞክራሲያዊ ሥርአትን ከአገራችን ምድር ለአንዴና ለሁሌም መጣል ያለብን ።

እነኝህን ከላይ የጠቀስኳቸው ያለፈው ታሪካችን ተመክሮዎች በመጠኑም ቢሆን የወደፊት አቅጣጫችን ምን መሆን እንዳለበት የጠቆሙ ይመስለኛል። እነኝህን ሀሳቦች ስብስብ አድርጎ የወደፊቱን አቅጣጫ በንድፈ ሀሳባዊ ግንዘቤ ደረጃ ሳይሆን በተግባርና በትግል ስልት ደረጃ ምን እንደሚመስሉ ጥቂት ሀሳቦችን ስንዝሬ ልለፍ። ከዚህም አንፃር ከቅንጅት እንደ ድርጅት፣ በቅንጅት ስር ከተሰባሰቡ ደጋፊዎች እንደ ግለሰብ ምን እንደሚጠበቅ አንድ ሁለት ቃላት ወርውሬ ላብቃ።

## 4. ከወሬ ወደ ተግባር፤ በጥራት ከማየት በፅናት ወደ መታገል ።

ካለፈው የአጭርና የረጅም ጊዜ ተመክሮዎች የምንቀሰመውን ትምህርት ከወሰድን በኋላ በመጀመሪያ ለማድረግ መወሰን ያለብን ብዙ ጊዜና ጉልበታችንን አሁን በሀገራችን ስላለው ኢዲሞክራሲያዊ ሥርአት በማሰብ ማጥፋት እንደሌለብን ነው። ይልቅ እሱን የሚተካውን ሥርአት በማሰላሰልና ለእሱም አስፈላጊ የሆነውን የአስተሳሰብ፤ ድርጅታዊና የስነ ልቦና እንዲሁም የስነ ምግባር ዝግጅቶች በማድረግና ለሱም በመሰራት ላይ ጊዚያችንን ማጥፋት እንደሚገባን ነው ። አሁን ያለው ሥርአት በስልጣን የሚቆየው የሕዝብን ይሁንታ አግኝቶ ሳይሆን በነፍጥ አስገድዶ መሆኑ ዛሬ የሚያከራክር ጉዳይ አይደለም። እንዲህ አይነት ሥርአት ደግሞ መሠረቱ የተረጋጋ አይደለም፤ መለወጡ አይቀርም። በዚህ ዙሪያ ዋናው የእንቅስቃሲያችን ትኩረት መሆን ያለበት እንዴት ነው ይህ ሥርአት በመውደቂያው ጊዜ ጥፋት አጥፍቶ እንዳይወድቅ ማድረግ የሚቻለው? የሚለው ብቻ ነው። ለዚህ ደግሞ ሁሌም እነሱ እራሳቸው ይህንን የማይቀረውን ውድቀታቸውን አውቀው፣ የመጣባቸውን የታሪክ ማእበል ፊት ለፊት ተጋፍጠው እነሱም ተጎድተው ሌላውንም ጎድተው ከሚያልፉ፣ አደብ ገዝተው የማይቀረው የለውጥ አካል እንዲሆኑ መምከራችንና መጥራታችንን፣ በዚህ ዙሪያም ተግባራዊ እርምጃዎች መውሰዳችንን መቀጠል ይገባናል። በሰላምና በድርድር፤ ብሄራዊ እርቅ፤ በአነስተኛ ዋጋ ክፍያ ሊመጣ የሚችል ለውጥ እስካለ ድረስ በግድ እርስ በእርሳችን ደም መፋሰስ ውስጥ መግባት አለብን ብሎ የሚያምን ለአገሩ የሚያስብ የወገን ሀይል አለ ብለን አናምንም። የእንቅስቃሲያችን ሞተር ጥላቻና ቂም በቀል አይደለም። ግባችን ያለፈውን በደል በአዲስ በደል መተካት አይደለም። ይህንን የቀረበለትን የዘንባባ ቅጠል እንደወትሮው መሬት ላይ ጥሎና ተሳልቆበት ለመቀጠል ካሰበ ደግሞ እኛም ባንሆን ሌሎች በጉልበት የመጣባቸውን በጉልበት ተቋቁመው አገሪቱን ከዚህ ኢፍታሀዊ ስርአት እንደሚገላግሏት ምንም ጥርጥር የለውም። ከዚህ አንፃር ሊባል የሚችል ነገር ቢኖር ከአሁን በኋላ ይህ ለውጥ

የሚመጣበት ጊዜ ሊዘገይ አለመቻሉ ነው። በቆየ ቁጥር አገሪቱና ሕዝቧ የሚከፍሉት እዳ በጣም ከባድ እየሆነ እየሄደ ነው። በጣም ከዘገየ ነፃነትና ዴሞክራሲን ብቻ ሳይሆን አገር የምንለውን ራሱን ሊያሳጣን ይችላል። ለዚህ ነው ከአሁን በኋላ በአልባሌ ወሬና ትርፋማ ባልሆነ የእርስ በእርስ ንትርክ የምናጠፋው ጊዜ የለንም ብዮ የማምነው። ትግላችን ለዴሞክራሲ ነውና እኛም ዴሞክራሲያዊ ነንና ብዙ ክርክር፤ ብዙ ውይይት ማድረጋችንን እንቀጥላለን። ግን የምናደርገው ውይይትና ክርክር ትርፋማ የሆነ፣ ቶሎ እየፈታን ውጤቱን በተግባር የምንቀይርበት እንጂ ማለቂያ የሌለው እውቀት ማበልፀጊያ ብቻ ሊሆን አይችልም። በዚህ ሂደት እውቀት፤ ስላለን የምንሞካሽበትና የምንኮፈስበት ግዑዝ እቃ ሳይሆን የዕለት ተዕለት ኑሮአችንን የምንቀይርበትና የምናሻሽልበት የስልጣኔ መሳሪያችን ነው። በዚህ ሂደት እውቀት የለውጥ መሳሪያችን ነው። እንጂ ከተግባር መደበቂያ፤ መኮላሸታችንን ምክንያታዊ ለማድረግ የምንጠቀምበት የግብዝነታችን ጭንብል እንዲሆን ልንፈቅድለት ፈፅሞ አይገባንም። በትግሉ ሂደት ብዙ በጣም ብዙ ችግሮች ይገጥሙናል። በትግሉ ውስጥ ባሉ አንዳንድ ሀይሎች ፀባይና አካሄድ ላንደሰት እንችላለን። ይህ ሁሉ ግን ትግሉን ለመሸሽ ምክንያት ሊሆን ፈፅሞ አይገባም። በእኔ እምነት እንዲህ አይነት አስቸጋሪ ፈተናዎች ሲገጥሙን በቶሎ ነገር አለሙን ሁሉ ትቶ የተደላደለ ሰላማዊ ኑሮዬን ለምን አልቀጥልም? ወደሚል ሽሽት የምንሄደው ብዙውን ግዜ ተሳትፎአችንን ለሌላ ለተበደለ ሰው ብለን የምናደርገው አድርገን ስለምንቆጥረው ነው። ሀቁ ግን ፍትህ ሲጓደል፣ መብት ሲረገጥ፤ ያልመረጥነው ሲገዛን የተበደልነው እኛ ራሳችን እንደ ግለሰብ ዜጎችና በጋራ እንደ አንድ አገር ልጆች ነው። ትግሉ ውስጥ መግባት ያለብን ሌላውን ነፃ ለማውጣት ሳይሆን ራሳችንን ነፃ ለማውጣት ነው። የመንግስትን ስልጣን በሃይል ይዞ፤ በአገሪቱ መንግስታዊ ተቋማት ፍፁም እየቀለደ፤ በፈለገ ግዜ ሊገድለን በፈለገ ጊዜ ሊያስረን የሚችል ስልጣን አለኝ ብሎ እንደልቡ ሊያደርገን የሚፈልግ መንግስት ባለበት እኛ እያንዳንዳችን ተገዢዎች (subjects) እንጂ ዜጎች አይደለንም። ይህን ሁኔታ ምንም ሳይታገሉት ዝም ብሎ መቀበል ከምንም ነገር ባላይ እራስን ማዋረድ ነው። የራስን የመኖር ትርጉም ነው የሚያሳጣው። ለዚህ ነው ይህንን ኢፍትሀዊነት ከዳር ሆነን እያየን ሰላማዊ ኑሮ እየኖርን ነው ለማለት የማይቻለን። ለዚህ ነው ይህንን ሥርአት ሁላችንም በቁርጠኝነት ብቻ ሳይሆን ነፃነቱን ከሚወድ ሰው በወጣ እልህ መታገል ያለብን።

ለትግላችን መነሻ የሚሆን ሰፊ ሕዝባዊ መሠረት የሚሰጡን ሀሳቦች ምን መሆን እንዳለባቸው ቀደም ብዬ ጠቅሸዋለሁ። ፍትህ ( justice )፤ ነፃነት ( liberty ) እና የዜጎች የፓሊቲከ እኩልነት ወይንም ዴሞክራሲያዊ የፓለቲካ ሥርአት ናቸው። በዚህ ትግል ውስጥ ከሚሰባሰቡ ሀይሎች የሚጠበቀው በሕዝብ ውሳኔ ለመገዛት ከልብ የመነጨ ቁርጠኝነት ነው። ይህ ደግሞ ጊዜያዊ የፓለቲካ ትርፍ ለማግኘት ሲባል ብቻ የሚያነበንቡት፤ ጊዜ አመቸን ስንል የምንጥለው ሀሳብ ሳይሆን ማህበረሰባችንንና የግል ህይወታችንን ጭምር በሚመለከት ያሉንን የተለያዩ መሰረታዊ አስተሳሰቦች ሁሉ የምናደራጅባቸው የአብሮ መኖራችን (እንደ አገርና የፓለቲከ ማህበረሰብ) ዋልታዎች ናቸው። እነኝህ ከሌሉን አገር የለንም። ግለሰባዊም ሆነ አገራዊ ማንነት የለንም። ያለ ነፃነት ሰው አይደለንም። ያለ ፍትህና የፓለቲካ እኩልነት ዜጎች አይደለንም።

እነኝህን ሀሳቦች ከጨበጥን በኋላ ወደ ግባችን ለመድረስ የሚያስፈልገን በዚህ ዙሪያ የተሰባሰበ ሰፊ አገራዊ እንቅስቃሴ አሁኑኑ መጀመር ወይንም በተናጠል የተጀመሩትን አሰባስቦና አጠናክሮ የራሳችንንና የአገራችንን ሰቆቃ እንዲበቃ ማድረግ ነው። በዚህ አገራዊ የዴሞክራሲ እንቅስቃሴ ውስጥ እነኝህን መሰረታዊ ሀሳቦች የተቀበለ ሀይል በሙሉ መካተትና የየራሱን አስተዋፅኦ ማበርከት አለበት። ዘፋኙ

ስለ ነፃነትና ስለ ዴሞክራሲ ማዜም አለበት:: የማህበራዊ ሳይንስ ምሁሩ ስለ ትግሉና ስለ ወደፊቱ ማህበረሰብ መፃፍ አለበት:: መሀንዲሱ በአዲሱ ስርአት ስለሚገነቡት ድርጅቶች አሁን ማሰብ አለበት፤ የትምህርት ባለሞያው ነፃነታቸው ለተረጋገጠላቸው ልጆቻችን የሚመጥን የትምህርት ሥርአት ከአሁኑ ማዘጋጀት አለበት፤ የእርሻ ባለሞያው ግብርናችንን ተብትቦ ከያዘው ኋላ ቀር የእርሻ ዘዴና የመሬት ሥርአት የሚነቀልበትን መንገድ መሻት አለበት፤ ባለሃብት ወገኖቻችን በዚህ ኢፍትሀዊ ስርአት ውስጥ ሆነውና ከመንግስት ጋር ተሞዳሙደው ስለሚያገኙት የማይገባ ጥቅም ሳይሆን ለሁሉም ባለሀብቶች እኩልና የተደላደለ ሜዳ በሚኖርባት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ውስጥ በሀቅ ተወዳድረው በአገሪቱ ሀብትና ሥራ የሚፈጥሩበትን መንገድ ከአሁኑ ማስላት አለባቸው:: ምክንያቱም፤ ውድ ወገኖቼ፤ እኛ ተባብረን ከታገልን እውነተኛ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን የምንፈጥርበት ጊዜ በፍፁም እሩቅ አይሆንምና:: እስከዚያ ግን የምናደርገው ትግል ማንንም የዴሞክራሲ ሀይል የሚያገል መሆን የለበትም:: ሀዘኔታችንና ቁጭታችን ከተበደሉት ውስጥ እየለየን እኛ በቅርብ ለምናውቃቸው ብቻ መሆን የለበትም:: በአዲስ አበባ ንፁሀን ዜጎች ላይ የደረሰውና የሚደርሰው ጭፍጨፋና ስቃይ የሚያንገበግበንን ያህል በኡጋዴን ሰላማዊ ዜጋችን ላይ የሚደርሰው የሰብአዊ መብት ረገጣ የዚያኑ ያህል ሊያመን፤ በእኩል ጉልበት ልንጮህለት በእኩል ሀይል ልንታገልለት ይገባል:: እኛን ከእስር ለማስፈታት የተደረገውን ትግል የሚመጥን ትግል በተለያዩ የኦሮምያ ክልል ወገኖቻችንና ዜጎቻችን ላይ የሚደረገውን አፈና እስራትና ግድያ የሚያወግዝ ትግል ማድረግ ይጠበቅብናል:: በጋምቤላና በደቡብ የተደረገውን ጭፍጨፋ ቀደም ብለን ባለፉት ሁለት አመታት ባሳየነው ቁጣና ሀይል አውግዘነው ቢሆን ኖሮ በአዲስ አበባ ላይ የደረሰው ላይደገም ይችል ነበር:: ስለዚህ ትግላችንን ማስተባበር አለብን ስንል የትግላችንም አድማስ ከአንድ የኢትዬጵያ ጫፍ እስከ ሌላኛው ጫፍ ድረስ የሚደረግ ማንኛውንም ኢዲሞክራሲያዊነትንና ኢፍትሃዊነትን በእኩልነት የሚታገል መሆኑን መቀበል ማለት ነው:: ይህም ማለት የምንፈጥረው ህብረት የወሬ ህብረት፤ በወረቀት ላይ የሚቀመጥ ንድፍ ሳይሆን የእለት ተእለት ትግላችንን የምናስተባብርበት መሆኑን ተቀብለን ነው መንቀሳቀስ ያለብን::

## 5. ከዚህ አንፃር ከቅንጅት እንደ ድርጅትና በቅንጅት ዙሪያ ከተሰባሰቡ ደገፊዎቻችን ምን ይጠበቃል?

ከዚህ በላይ በአነሳኂቸው ነጥቦች ላይ አጠቃላይ ስምምነት ካለ የአድማጮቼን ትዕግስት ላለመፈታተን ከዚህ አንጻር ከቅንጅት እንደ ድርጅትና በዙሪያው ከተሰባሰበው ሰፊ የድጋፍ ሀይላችን ምን ይጠበቃል? በሚለው ጥያቄ ላይ አንድ ሁለት ሀሳቦችን ሰንዝሬ ላብቃ:: በመጀመሪያ ከምንም ነገር በላይ ይጠቅመናል ብዬ የማስበው ከዚህ በላይ ላነሳኂቸው አላማዎች ፍጽም ቁርጠኝት ( determination ) ከዚህ አይነት የውስጥ ቁርጠኝነት የሚመጣ በራስ መተማመን ( confidence ) እና ከዚህ አይነት በራስ መተማመን የሚወለድ ትሁትነት ( modesty ) ናቸው:: እነኝህን የተያያዙ ጠባያት የትግሉን ቃና (tone) መስመር በማስያዝ የትግሉን ሂደት ከግባችን ጋር የሚያቆራኙት ጠንካራ ክሮች ናቸው:: ቁርጠኝነት የሚመጣው ከአላማችን ትክክለኝነትና ለዚህ አላማ ማለትም በፍህታዊና በዲሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ ለመኖር እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ ሕዝብ ብቃት ያለን መሆኑን ከልባችን በማመናችን ብቻ ሳይሆን፣ በተለይ እንደ ሕዝብ በግንቦቱ ምርጫ፣ ማየት ለሚፈልግና ከጥላቻና ከእብሪት የጸዳ ክፍት አዕምሮ ላለው ሁሉ፣ ያሳየን በመሆኑ ነው:: አላማችን እውነት በመሆኑ ደግሞ ከእውነት ጋር ጸብ የለንም፤ እውነትን ሁሌም የምንሻ በመሆናችን በትግሉ ሂደት ለምናደርገው ስህተት (ስህተት ማድረጋችን አይቀርም) መታረምን ሁሌም የምንፈልግ ለእርምት የተመቻቸን፤ ስህተታችንን አርመን ወደ ላቃ እውነት ለመሄድ ሁሌም የተዘጋጀን እንጂ አንዱን ስህተታችንን ለመደበቅ ስንል ሌላ የስህተት

ማጥ ውስጥ ለመግባት የምንፈቅድ ግብዞች ልንሆን ከቶ አይቻለንም:: በራስ መተማመናችንና ልበ ሙሉነታችንም የሚመነጨው ከዚህ የአላማችን እውነትነት ነው:: አላማችን እውነት ነው ማለት ሁልጊዜም የምናደርገው ነገር ትክክል ነው ማለት ግን አይደለም:: ለዚህም ነው ሁሌም ለመሻሻል፤ ሁሌም ለአዲስ እውቀት ክፍት መሆን ያለብን:: በስራ ላይ እስካለን ድረስ ልንሳሳት እንችላለን:: እኛ ያላየነውን እውነት ሌላው፣ አንዳንዴም ባላንጣችን ሳይቀር ሊያየው ይችላል እና ከባላንጣችን እንኳን ሳይቀር ለመማር ክፍት የሆነ አእምሮ ያስፈልገናል:: የአላማችንና የግባችን እውነትነት በፍጹም ከእኛ በላይ አዋቂ ወይም ከእኛ በላይ ትክክለኛ የለም ወደሚል ትእቢት ሊወስደን አይገባም:: ለዚህ ነው ትሁትነት ወይም (modesty) ሊኖረን ይገባል ያልኩት:: ትሁትነት ግን ፍርሃት ወይም በፍጹም ጥርጣሬን በሚያመለክት ወይም በሚጋብዝ መልኩ አይደለም:: በራስ ከመተማመን የሚመጣውና እምንታዊውን ሰብአዊ እሴት ማለቴ ነው::

ከዚህ አንፃር ድርጅታዊ ትሁተኛነትን በሚመለከት በምርጫ 97 ወቅት በተደጋጋሚ ይነሳ የነበረ አንድን አባባል በምሳሌነት ልጥቀስ:: ቅንጅት ከተመሰረተ በኋላ በአስደናቂ ፍጥነት የሕዝቡን ቀልብ እየሳበ ሲሄድና በምርጫው ወቅትም ሕዝቡ ቅንጅትን በመደገፍ በራሱ ተነሳሽነት ብዙ እርምጃዎችን ሲወስድና ቅንጅትም በእውነት ካለው ድርጅታዊ አቅም በላይ በስሙ ብዙ ነገሮች ሲከናወኑ ሲታይ፤ ቅንጅት መንፈስ ነው የሚለውን አባባል በቅንጅቱ የውህደት ቀን ብርቱካን ባደረገችው ንግግር ተጠቅማበት ከሞላ ጎደል የራሱን ህይወት ይዞ ቋሚ መፈክር ሆነ:: ይህንን አባባል የተለያዩ ሰዎች በተለያዩ መንገድ ተርጉመውታል:: የቅንጅት እንደዚህ በፍጥነት ተሰሚነት ማግኘት ያሳሰባቸውና ያልወደዱ የቅንጅት ባላንጣዎች አባባሉን ቅንጅት ለራሱ መለኮታዊ የሚመስል ስሜት ለመፍጠር የሚፈለግ መመፃደቅ አድርገው ወሰዱት:: ይህን አባባል የሚጠቀሙበት በቅንጅት ቢሮ አካባቢ የነበሩ አባሎቻችን ግን አባባሉን የወሰዱት በሁለት መልኩ ነበር:: አንድም የቅንጅትን እውነተኛ ድርጅታዊ ድክመት ያውቁት ስለነበረና በዚህ ድረጅታዊ ድክመቱ የሰራቸውን ግዙፍ ስራዎች  በመገረም በመመልከትና ቅንጅት በእውነተኛ ድርጅታዊ ጥንካሬው ያደረገው ድርጊት ሳይሆን፣ ሕዘቡ በራስ መነሳሳት መንፈስ ያደረገው ብዙ ጊዜ ከቅንጅትም ድርጅታዊ እውቅና የወጡ አዎንታዊ ስራዎች ይሰሩ እንደነበር በመቀበል ነው:: ሁለተኛውና ከዚያም ያለፈው ግን ይህ የቅንጅትን ድርጅታዊ መልክ የያዘው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ከቅንጅትም ያለፈ ሀይልና እንድምታ ያለው መሆኑን ለማመልከት ነበር:: ቅንጅት በጊዜው የሞከረው የሕዝቡን የነጻነትና የዴሞክራሲ ጥማት ለማርካት ነበር:: ይህ የሕዝብ የነጻነትና የዲሞክራሲ ጥማት ከቅንጅት ጋር እንደተያየዘ መቀጠል የሚችለው ቅንጅት ለነጻነትና ለዲሞክራሲ ያለውን ወገንተኛነት፣ ለዚያ ትግል ያለውን ቁርጠኝነት ይዞ እስከቀጠለ ድረስ አብሮት የሚሄድ እንጂ፤ ከዚህ መስመሩ ካፈነገጠ፤ እምነቱን ሸጦ ለስልጣንና ለሌላ ጥቅም ካደረ፤ በውስጠ-ድርጅት እንቅስቃሴው ይህንን ለህዝብ በአደባባይ የገባውን ጠንካራ ዴሞክረሲያዊ እምነቱን ከላንጸባረቀ በማንኛውንም ጊዜ በሕዝቡ የተወደደውን ያህል፤ የሕዝቡን የዲሞክራሲና የፍትህ ጥማት ከስሙ ጋር እንዲያቆራኘው ሕዝቡ የፈቀደለትን ያህል፤ በቀላሉ አውልቆ ሊጥለው የሚችለው መሆኑን በቅጡ የተገነዘብንበት ነበር :: የቅንጅት አመራር ይህን የሕዝብ ስሜትና ፍለጎት ጥዬ ፓርላማ ገብቼ፤ ሱፍ ኮትና ክራባት አድርገን፤ የተከበሩ እየተባባልን ከምንሸነጋገል ዘብጥያ ብንወርድ ይሻለናል ብሎ፤ ዘብጥያ ሲወርድና ከ20 ወራት በኋላ ሕዝቡ ልክ እንደቀድሞው የዲሞክረሲ ፍላጎቱ ሰብአዊ መግለጫ አድረጎ የተቀበለንም ያንን እምነቱን በእውነትና በምንችለው መጠን ለማንጸባረቅ በመሞከራችን ነው:: ይህንን መንፈስ በሌላ የቀይረን እለት ያ “የቅንጅት መንፈስ”  የተባለው ነገር የሌላ ድርጅት ስም ወይንም እውነተኛውን «የነጻነትና የዲሞክረሲ መንፈስ » የሚለው ስሙን ይይዛል :: ይህንን ማወቅና መረዳትን ነው

ድርጅታዊ ትሁትነት የምለው፡፡ እንዲህ አይነት ትሁትነት ያለው ድርጅት ሌሎችንም አይንቅም፡፡ ከሌሎች ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች ጋር ለመስራት ክፍት ነው፡፡ ከሌሎች ጋር በሚሰራበት ጊዜም የሚሸከመውን ሀላፊነት የሚያዬው "እኔ ከሌሎች ስለምበልጥ" የተሻለ ቦታ ሊሰጠኝ ይገባል ከሚል፤ ወይም እኔ ለትግሉ ብዙ ያበረከትኩ ስለሆነ ከኔ የተሻሉ ሌሎች አዳዲስ ሰዎች ቢኖሩም ቦታውን በእርስተ ጉልትነት መያዝ ያለብኝ እኔ ነኝ ከሚል፤ ወይንም ብዙ በመታሰሬና አባሎቼ ብዙ መስእዋትነት ስለከፈሉ፤ የስልጣን ቦታ እንደ ደም ካሳ ለእኔ ይገባኛል ከሚል ከንቱ መከራከሪያ አይደለም፡፡ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመገንባት በሚደረገው ትግል ሁሉም በችሎታውና በአቅሙ የተሻለ አስተዋጽኦ የሚያደርግበት ቦታ መመደብ አለበት፡፡ ቅንጅት እንደ ድርጅት ወይም የቅንጅት አመራሮች እንደ ግለሰብ ዲሞክራሲን ለማምጣት ከሌሎች ሀይሎች ጋር በሚደረግ ትግል ድሉን በአጭር ግዜ ለማምጣት፤ የሃገራችንን ሰቆቃ ጊዜ ለማሳጠር፤ በየትኛው የሀላፊነት ቦታ ብናገለግል ነው የሚሻለው ብለን፤ ለዚያ የሚመጥን ቦታ ይዘን ለትግሉ አስተዋጽኦ ማድረግ ብቻ ነው ፍላጎታችን ሊሆን የሚችለው፡፡ የስልጣኑን ነገር በኋላ፤ ከሌላው የምንለይበት አቋም ካለን ይህንን ለሕዝብ አቅርበን፣ ሕዝቡ ይገባቸዋል የሚለንን በድምጹ ይሰጠናል፡፡ በትግሉ ሂደት ለከፈልነው ወደ ፊትም ለምንከፍለው መስእዋትነት ግን ዲሞክራሲያዊና ፍታዣዊ ስርአት በሀገራችን ተመስርቶ ከማየት ባሻገር የሚገኝ ትልቅ ክፍያ አይኖርም፡፡ በተለይ ከአሁን በኋላ ከመንግስት ሥልጣን መያዝ የሚገኝ ክፍያ መቼም ይኖራል ብዬ አልገምትም፡፡

እነኝህ ከላይ በአጭሩ ካነሳኋቸው ባህርያት ጋር የተያያዘውና ከቅንጅት የሚጠበቀው ሌላ ነገር፤ በተለያዩ ምክንያቶች በእጃችን የገባውን የሕዝብ የዲሞክራሲ ፍላጎት ምልክትነታችንን ይዘን ሕዝቡ የጣለብንን እምነት ጠብቀን ለመቀጠል የሚያስችለን በዴሞክረሲና በፍትህ ጥያቄ ላይ ያለን ግልጽነትና የአላማ ቆራጥነት በሌሎች ጥቃቅን የእለት ተእለት የፖለቲከ ጥያቄዎችና የግለሰብ ንትረኮች እዳይደበዝዙ መጠንቀቅ ነው፡፡ ሕዝብ ያዬውን ይታዘባል፡፡ ጥልቅ አላማ ይዘን በትናንሽ ጉዳዮች ይህን አላማ ልናረክሰውና ልንጥለው አይገባም፡፡ በሌላ አነጋገር ቆምንለት ለምንለው አላማ ትልቅ ክብር፤ እውነተኛ ክብር ሊኖረን ይገባል፡፡ ትግሉን እንመራለን ወይም ለትግሉ ቀዳሚ ሚና እንጫወታለን የምንል ሰዎች ለዚህ አላማና ለሚጠይቀው የእለት ተእለት ስነ ምግባር ከፍተኛውን ከበሬታ በተግባር ካላሳየን በአጠቃላይ ማሕብረሰብም ዘንድ አላማውን በሚመለከት የመናቅና ተስፋ የመቁረጥ ስሜት እንዲነግስ ብቻ ነው የምንረዳው፡፡ ለአላማው ቀድሞውንም ምንም ክብር የሌላቸውና ፖለቲካንና የጋራ ማህበራዊ ኑሮን ከራሳቸው የግል ጥቅም ባሻገር ለመመልከት አቅሙም ፍለጎቱም ለሌላቸው የዴሞክራሲ ጠላቶች በዲሞክራሲ ሀይሎች ውስጥ የሚታይ አላማን የሚያረክስ ተግባር እጅግ ነው የሚያስደስታቸው፡፡ ምክንያቱም ትልቁ ድክመታቸው ሞራል-ቢስነታቸው መሆኑን ስለሚያውቁ፤ በዚህ አይነት ከፍተኛ የሞራልና የአላማ ደረጃ ሊገጥሙን አይቻላቸውም፡፡ ቢሳካላቸው ሁላችንም አንድ አይነት የሞራል ቁሻሻ ውስጥ ያለን መሆኑን ማሳየት ነው የሚፈልጉት፡፡ ይህ ከተሳካላቸው ከዚያ በኋላ ትግሉ የሚሆነው እነርሱ በሚወዱትና አቅም ባላቸው የእለት ተቀን የፖለቲከ ጨዋታ ማን ከማን ይበልጣል የሚል መርህ አልባ መንገታገት ነው የሚሆነው፡፡ ስለዚህም የአላማ ግልጽነትና ጽናት፤ የፖለቲካ ተግባራችንንም ከዚህ ከፍተኛ አላማችን ጋር በማጣጣም መልኩ ብቻ ማስኬድ ለስኬታችን ወሳኝ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ታሪካዊ ወቅት ቅንጅትና አባሎቹ በላያቸው ላይ የወደቀው ሀላፊነት በዲሞክራሲ ትግሉ ወቅት መታዬት ያለበት ቀደም ብዬ የጠቀስኳቸው ባህሪያት ከማንም በላይ

በድርጅት አመራርና አባላት ላይ መንጸባረቅ ያለበት ነው። የዲሞክራሲ ፖለቲካ የሚጠይቀውን ትሁትነትና ስልጡንነት (civility) ማንጸባረቅ ለዋና አላማችን ያለንን ጽናት የምናሳይበት አንዱ የእለት ተእለት መሳሪያችን ነው። ትግላችን ለፍትህና ለዲሞክራሲ ነው ስንል ይህንን የምንሰብከው ማንኛውም አካል እንዲያምነን ያስፈልጋል። ይህንን አመኔታ የምናገኘው ደግሞ አላማችን ለዲሞክራሲና ለፍትህ ነው እያልን እየደጋገምን በመናገራችን አይደለም። በወሬና በንግግር ቢሆንማ የኢትዮጵያን ራዲዮና ተሌቪዥን ለሰማ ከኢሕአድግ በላይ ዴሞክራሲያዊነት፣ ከአቶ መለስ በላይ ለህግ የበላይነት ተቆርቋሪ ላሳር ይሆን ነበር። በዛሬ ጊዜ ሁሉም ነገር የሚመዘነው እና የሚለካው በተግባሩ ነው። አላማችንና ግባችን ለፍትህና ለዲሞክራሲ ነው ካልን በእለት ተእለት የፖለቲካ አካሄዳችን እነኝህን ባህሪያት ማንጸባረቅ ይጠበቅብናል። ቃላችን በተግባራችን ሲገለጽ ብቻ ነው ሰው ከምር ሊወስደን የሚገባው። እርስ በእርሳችን (ድርጅታችን ውስጥ ወይም በድጋፍ ድርጅቶች ) ወይንም በትግሉ ሂደት አብረን ልንጓዝ ከወሰንናቸው ሀይሎች ጋር በሚኖረን ግንኙነት ለአጭር ጊዜ የፖለቲክ ትርፍ ማግኛ ብለን ሰውን ከመጉዳት መራቅ፣ ከአሉባልታ መሸሽ፣ ለእውቅት ክፍት መሆን፣ ለስራ መትጋት፣ የባላንጣን ሀሳብ ማዳመጥ ወዘተ.. በአጠቃላይ የሰለጠነ የፖለቲካ ውይይትና የሰለጠነ ፖለቲካ የሚጠይቀውን ጨዋነት ማሳየት ይጠበቅብናል። በዴሞክረሲ ፖለቲካ የበላይነት የሚገኘው በክፍት ውይይት ሕዝብን በማሳመን እስከሆነ ድረስ ወደፊት ሥልጣን ላይ ለመውጣት ፍላጎት ላላቸውም ይህንን የፖለቲካ ባህል ከአሁኑ መልመዱ ይጠቅማቸዋል። ልንመሰረት የምንፈልገው የፖለተካ ስርአት ለአገራችን አዲስ ነው። በድሮ ያረጀ የፖለቲካ ሽርና ተንኮል ቀድሞ ለመገኘት በጣም ይቸግራል። ስለዚህ እኛ ቅንጅቶችና ደጋፊዎቻችን ለዚህ አዲስ የፖለቲካ ስርአት የሚመጥን የፖለቲካ ባህል ይዘን መገኘት ይጠበቅብናል።

ይህ አዲስ ባህል ከጥላቻ የራቀ ፓለቲካም ነው። ጥላቻና ፍርሀት እኛ የሰው ልጆች ከሌሎች እንስሳት የምንጋራው የደመ ነፍስ ስሜት ነው። ቀላል ነው። ብዙ ማሰብና ማሰላሰልን አይጠይቅም። ይህ ስሜት በሌላ ወገን ባለው ሀይል ላይም ተመሳሳይ የሆነ ስሜት ወዲያውኑ ስለሚፈጥር እራስን ለማዳን የሚቻለው ሌላውን በማጥፋት ብቻ ነው። በዚህ ስሜት እየተነሱ ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንደዚሁም በሰላም አብሮ ለመኖር የሚችል የሰው ልጆች ማህበረሰብ መፍጠር ያዳግታል። ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት ሊበራል ዴሞክራሲያ ፓለቲካ ( political liberalism ) ብዙ ጠንካራ የሃይማኖትና የባህል ልዩነቶች ባሉባቸው ማህበረሰባት ውስጥ የጋራ የፓለቲካ ህይወትን በሰላምና በፍትህ ለመምራት የሚረዳ መሳሪያ ነው። ይህ ስርአት እንዲሰራ ከፈለግን ከኛ ለተለየው ጥላቻ ሳይሆን ሊኖረን የሚገባው በተቻለ መጠን የሱን አመለካከት ለመረዳት፣ የእሱን ፍርሃት ለማርገብ መሞከር፣ ለእሷ የተበደልኩ ስሜት ሃዘኔታን ( sympathy ) ማሳየት፣ ግን በተቻለ መጠን ለሁሉም ፍትሃዊ የሆነ መፍትሄ ለመፈለግ መጣር ነው። ይህ አይነት የፓለቲካ አካሄድ ከሌላው ይልቅ የበለጠ የሚያደክምና ብዙ ሥራ የሚጠይቅ ነው። የሰነፍ ፖለቲካ አይደለም። ከራስ ስሜቶች ባላይ የሌላውን መረዳት ስለሚጠይቅ እንደ አምባገነንነት ለሁሉ ነገር ወጥና ቀላል መልስ መስጠት ( ለምሳሌ ጉልበት ) አይቻለውም። ብዙ ማንበብ፣ ብዙ ማድመጥ፣ ብዙ መወያዬት ይጠይቃል። ይህንን ከጥላቻ የጸዳ የፍቅርና የመረዳዳት ባህልና አካሄድ ነው በቅንጅት ዙሪያ የተሰባሰብን ሰዎች ሁሉ ማበልጸግ የሚጠበቅብን። በሌላ በኩል ለሚገጥመን የጥላቻ ፖለቲካ በመርህ ላይ የተመሰረተ የፍቅር መልስ እንመልስ ስንል ግን በምንም አይነት ከፍርሀትና ጊዜው ለሚፈጥረው የትግል ጥያቄ ተገቢውን መልስ ለመስጠት ከሚሸሽ ወኔ-ቢስ ስሜት የሚመጣ እንዳልሆነ ከወዲሁ ግልፅ አድርጌ ማለፍ እፈልጋለሁ። የፍቅር ፓለቲካ የደካሞች፣ የፈሪዎችና የወገብ የለሾች ፓለቲካ አይደለም። በመርህ ላይ የተመሰረተ፣ ትግሉ የሚጠይቀውን

መስዋትነት ለመክፈል ዝግጅ የሆነ፤ በስሜት ሳይሆን አስቦ የሚንቀሳቀስ፤ለሚደርስበት ጫና መልሶ ተገቢውን ጫና ማሳረፍ የሚችል ነው።

ቅንጅት በመሰረታዊ ጉዳዮች ተስማምተን የትግል አጋርነት ፈጥረን አብረናቸው ከምንታገላቸው ሀይሎች ጋር በሚኖር ግንኙነት እንዲህ አይነቱን አጋርነትን ትርፋማ በሆነ መንገድ ለማሰራት የሚያስችለውን ትዕግስትና ፍላጎት በማሳየት በትጋት መስራት ይጠበቅበታል። ለእንዲህ አይነት የተባረከ ዴሞክራሲያዊ ትግል ከምር መቆሙን ለማሳየት ህብረቱን በመፍጠር ሂደትም ሆነ፣ ህብረቱ ከተፈጠረም በኋላ በሚደረገው እንቅስቃሴ ከፊት መቆም፤ ከእንዲህ አይነት ትግል ለማፈግፈግ የሚሞክሩትን እንዳይሸሹ ማበረታታት፤ ጥቃቅን በሆነና በሁለተኛና በሶስተኛ ደረጃ በሚታዮ ጉዳዮች ላይ በማተኮር የትግሉን አቅጣጫ ለማሳት የሚሞክሩ ሀይሎችን አይናቸውን ከዋናው የጋራ አላማ ላይ እንዳያነሱ በመማፀን፣ ትኩረታቸውን በዋናው ጉዳይ ላይ እንዲያደርጉ መገፋፋት፤ በዴሞክራሲያዊ ትግሉ የሚሳተፋ የተለያዩ ሀይሎች የሚያነሷቸው፣ (ከህብረቱ መሰረታዊ አቋሞች ውጭ ቢሆኑም) ለእነሱ አስፈላጊ የሆኑ ጥያቄዎችን ሳያጣጥሉ ወይንም ሳያናንቁ በነኝህ ጉዳዬች ላይ ያሉ ልዩነቶች በድርጅት ደረጃ ሳይሆን፣ ከሕዝብ ፊት ቀርበው በሕዝብ ድምፅ የሚፈቱ መሆናቸውን በአፅንኦት በመግለፅ እንዲህ አይነት ልዩነቶች የህብረት ዴሞክራሲያዊ ትግሉን እንዳያጨናግፉ ማግባባት፤ ባጠቃላይም ቅንጅትና ደጋፊዎቹ ለተባበረው የዴሞክራሲና የፍትህ ትግል ፍፁም አዎንታዊ የሆነ አስተዋፅኦ ለማድረግ በመርህ ላይ የተመሰረተ ጠንከራ አቋም መያዝ ይጠበቅብናል። ለዚህ ዋናው ምክንያት እነኝህን የህብረቱ መነሻ መርሆዎች ብለን ያስቀመጥናቸው ቁም ነገሮች ለሌሎቹ ከዚያም በላይ ለሆነ ግብ መንደርደሪያ ሃሳቦች እንኳን ቢሆኑም ለእኛ ግን ዋናው ግቦቻችን ናቸውና፣ በእነኝህ መነሻ ሀሳቦች ላይ ተነስቶ የሚመሰረት ሥርአት ከማንም ባላይ ለእኛ ትልቁ ድላችን ነው። ትክክለኛ የስልጣን ትግል የሚደገረው ይህ ሥርአት ተቋቁሞ ከዚያ በኋላ የተለያዩ የፓለቲካ ደርጅቶች የፓለቲከ ስልጣን ለመያዝ ሀሳባቸውን ለሕዝብ በማቅረብ ሕዝብ በሚያደርገው ምርጫ ነው። ያን ግዜ ስልጣን ላይ የሚወጣው ማን እንደሆነ በእውነቱ አይታወቅም። አሁን ካለንበት ቦታ ላይ ሆነን ስናየው ደግሞ በእውነቱ ማን መሆኑ ያን ያህል ሊያስጨንቀን አይገባም። ምክንያቱም በሕዝብ ፈቃድ ስልጣን ላይ የሚመጣው ሀይል ስራውን በአግባቡ ካልሰራ በሚቀጥለው ምርጫ መባረሩ አይቀርም። መርጠን ያስቀመጥነውን መጥፎ መንግስት መርጠን እናወርዳዋለን ወይንም በሌላ እንተካዋለን። ይህ ስርአት ገቢር እንዲሆን አሁን የምናደርገው ትግል ግን በምንም አይነት የስልጣን ትግል አይደለም፤ እንደዚያ አይነት መልክ እንዲይዝም በፍፁም ልንፈቅድለት አይገባም። ከሕዝብ ፈቃድ ውጭ የሚገኝን ምንም አይነት ሥልጣን ምንም አይነት እውቅና ልንሰጠው አይገባም።

በመጨረሻም ቅንጅት እንደ ድርጅትና ደጋፊዎቹ በሙሉ ልንረዳውና ሁሌም ከልባችን ልናወጣው የማይገባን አንድ ነገር አለ። ይከውም ይህ ትግል ስላለፈው ሳይሆን ስለ ወደፊቱ መሆኑን ነው። ይህ ጉዳይ በምንም አይነት ብዥታ ውስጥ ሊከተን የማይገባ ለተባበረ ዲሞክራሲያዊ ትግሉ ደግሞ አስፈላጊ የሆነ እሳቤ ነው። ይህንን ጉዳይ ከሁለት ከተያያዙ ጉዳዮች ጋር አስደግፌ ላቅርበው። በመጀመሪያ ትግሉ ላለፈው ሳይሆን ስለወደፊቱ ነው ስል እነኝህን የትግላችን አንኳር ጉዳዬች ያልናቸው የፍትህና የዴሞክራሲ ጥያቄዎች ባለፈው ታሪካችን የኖርንባቸውና በአንድ አጋጣሚ ያጣናቸውን አሁን ያንን ስርአት ለማስመለስ የምናደርገው ትግል አለመሆኑን ለማሳየት ነው። እንዲህ አይነት ሥርአት በታሪካችን ኖሮን አያውቅም። ስለዚህ ለአገራችን አዲስ ነው። ይህ ማለት ግን ጥያቄዎቹ አዲስ ናቸው ማለት አይደለም። ፍትህ በሌለበት ሁሉ በአንድ መልኩ ወይንም በሌላ የፍትህ ጥያቄ መነሳቱ

አይቀርም። እንደ ፓለቲካዊና ማህበራዊ ሥርአት ግን ፍትህን መሰረት ያደረገ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ኖሮን አያወቅም። ስለዚህም በሌሎች ጥያቄዎች ላይ ታሪካችንን እያነሳን ልንወዛገብ ብንችል እንኳን ይህንን አዲስ ሥርአት በመፍጠር ሂደት እንዲህ አይነት ውዝግብ ብዙ አይጠቅመንም። ታሪካችንን ማወቅ የሚገባን፤ በታሪከችን ዙሪያ መወያዬት የሚጠቅሙን ብዙ ቁም ነገሮች ይኖራሉ። ግን የህን አዲስ ሥርአት በመፍጠር ዙሪያ ያንን የታሪክ ሸክም ብንጨምርበት የበለጠ መንገዱን ያወሳስበው እንደሆን እንጂ አንድም ጋት ወደፊት አይወስደንም። የደርግም ሆነ ከዚያ በፊት የነበሩት የአፄ ስርአቶች ፍትህን ማእከል ያደረጉ ዴሞክራሲያዊ ስርአቶች አልነበሩም። ስለዚህ ዴሞክራሲያዊ ትግሉ እነኛን ሥርአቶች የሚናፍቅበት ምንም ምክንያት የለውም። በሌላ መልኩ ደግሞ አሁን ያለንበት ኢፍትሀዊና ኢዴሞክራሲያዊ ሥርአት አስከፊነት የቀድሞዎቹን ሥርአቶች በድንገት ቆንጆ አያደርጋቸውም። ሁሉም በራሱ የታሪክ ወቅት በሰራው ስራና ባስገኘው ፋይዳ መመዘን አለበት። ለመመስረት የምንታገልለት ሥርአት ሁሉን አይነት ኢፍትሀዊነትን፤ ሁሉንም አይነት ኢዴሞክራሲያዊነትን የሚታገልና የወደፊቷን ኢትዮጵያ በእውነተኛ የፍትህና የዴሞክራሲ መሰረት ላይ ለማቆም ነው። ለምንም አይነት ኢዴሞክራሲያዊነት፤ ምንም ተከናንቦ ይምጣ የምንቀበለው ሊሆን አይችልም። ከዚህ ከአዲሱ ሥርአት ጋር አብሮ እንዲበለፅግ የምንፈልገው የአገር ፍቅር ለሰው ልጅ በአጠቃላይ በተለይም ደግሞ ለዜጎቹ ክብር ያለው መሆን አለበት። በአገር ፍቅር ስም በአገር አንድነት ስም የሚመጣ ኢፍትሃዊና ኢዴሞክራሲያዊ ስርአት በምንም አይነት የሃገር ፍቅር ያለው ስርአት መሆን አይችልም። ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ሃገር ማለት በፍትህ ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ማህበረሰብ ነው። ለዚያ ማህበረሰብ አባላት ፍትህን የሚነፍግ መንግስት በምንም አይነት የዚያ ሃገር ፍቅር አለኝና ለሃገር ፍቅር ስትሉ ግፍን ተቀበሉ፣ የአገዛዝ ስርአቱን ደግፉ ቢለን ጆሮ ልንሰጠው አይገባም። የዝያኑ ያክል በሃገር ፍቅርና አንድነት ስም ዴሞክራሲያዊ ትግሉ በምንም አይነት የዴሞክራሲና የፍትህ መስመሩን ሊስት አይገባም።

ከእዚህ ጋር የተያያዘው ሁለተኛው ነጥብ የታሪክ ጠባሳዎችን ወደፊት ልንፈጥር የምንፈልገውን የዴሞክራሲ ስርአት መያዥያ እንዳያደርጉት ማድረግ የሚገባን ጥንቃቄ ነው። ዛሬ የምንኖር ሰዎች ዋናው ትኩረታችን መሆን ያለበት ፍትህ እንዳይዛባ፣ ዛሬ መብቶች እንዲከበሩ፣ ዛሬ የወለድናቸው ልጆቻችን ነገ ነጻነት የሌለው ኑሮ እንዳይኖሩ ነው። ታሪካችንን በሚመለከትም ሊኖረን የሚገባው ግንዛቤ በታሪክ የታየው ኢፍትሀዊነት ዛሬ እንዳይደገም ነው። ከሁሉም ነገር በላይ መጠንቀቅ ያለብን የታሪካችን ጠባሳዎች ዛሬና ነገ መፍጠር ያለብንን ከነኛ ጠባሳዎች የፀዳ ስርአት ለመፍጠር እንቅፋት እንዳይሆኑብን ነው። ቀደም ብዬ እንዳልኩት ከታሪካችን መማር አለብን። በተለይ ለፍትህ እና ለዴሞክራሲ ሲደረጉ ከነበሩት ትግሎች ታሪክ መማር ስህተቶቻችንን እንዳንደግም ይረዳናል። ግን ሁሉንም ነገር ከታሪክ አንፃር ብቻ በማየት የታሪክ ቁርሾዎችን በማስታወስ፤ ቁስሎችን በመነካካትና ጥርጣሬዎችን በመፍጠር ሊኖር የሚገባውንና የወደፊት ህይወታችንን የሚወስነውን የጋራ የዴሞክራሲ ትግላችንን እንዳያደናቅፍብን በእጅጉ መጠንቀቅ ይኖርብናል። በታሪክ በዳይና ተበዳይ ከነበረ ያሁኑ ትውልድ የበዳይም የተበዳይም ዝርያዎች ከዚያ ታሪክ ይማራሉ ብለን ማመን አለብን። በተለይም አሁን ያለንበት ሁኔታ ኢፍትሀዊ ከሆነ፤ ይህ የታሪክ ትምህርት ፍትህ ያጡትን ሁሉ የሚያስተባብር መሆን ይችላል። የዚያኑ ያህል የታሪክ ጠባሳዎች ለዛሬና ለወደፊት ቁርሾ መወጫዎች ሊሆኑ በፍጹም አይገባም። እንዲህ አይነት አመለካከት ማለቂያ የሌለው የኢፍትሃዊነት አዙሪት ውስጥ ነው የሚከተን። በእዚህ አመለካከት ጉዳዩ ፍትህ ማስፈን መሆኑ ይቀርና ስልጣን የረጋጭነት ተራ ማያዣ ይሆናል። ይህ አመለካከት ባለበት የፖለቲካ ስልጣን ትግሉም የዛኑ ያህል ሃይለኛና ጨካኝ ይሆናል።

በእዚህ ሁኔታ ፍትህ የሰፈነበት ዴሞክራሲያዊ ስርአት፣ እንዲሁም የተረጋጋ ሃገርም ሊኖረን አይችልም:: ከእንደዚህ አይነት አዙሪት ለመውጣት እንዲቻል ነበር ቅንጅት ኢህአዴግን የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ አካል እንዲሆን በተደጋጋሚ ጥሪ ያቀረበለት:: ለእዚህ ነው ቅንጅት የብሄራዊ እርቅ አጀንዳ እንደ ዋናው አጀንዳው ይዞ የታገለው:: ለእዚህ ነው አሁንም ከምርጫ 97 በኋላም ኢህአዴግ ለስልጣን ብሎ ያደረገውን ጭፍጨፋና ወደር የሌለው አፈና፣ የእኛን የቅንጅትን አመራሮችን ያደረሰብንን መጠን የለሽ የእስራት በደል፣ በሽዎች የኦሮሞ የጋምቤላ የኦጋዴን የደቡብ የአማራ የትግራይ ወዘተ ዜጎቻችን ላይ ያደረሰውን አስከፊ በደል እየቆጠቆጠንና እያመመንም በእዚች የመጨረሻ ሰአትም ኢህአዴግ ልቦና ገዝቶ ከቂም በቀልና ካለአስፈላጊ የወገኖቻችን ስቃይ የፖለቲካ ህይወታችንን ወደ ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ መስምር ለመክተት በምናደርገው ትግል የመፍትሄው አካል እንዲሆን የምንወተውተው:: የጥላቻና የቂም በቀል፣ የጉልበትና የትእቢት፣ የድንቁርናና የኋላቀር የፖለቲካ ፋይሎች ተዘግተው የፍትህ ፣ የዴሞክራሲ፣ የስለጡን ፖለቲካ መስመር ውስጥ እንግባ የምንለው:: ይህንን አሻፈረኝ ብሎ በትግላችን ያለውን ሁኔታ ቀይረን የምንፈጥረው የፍትህና የዴሞክራሲ ስርአት ግን በኢህአዴግ እልህና ጥላቻ ተመርዞ ወደ ሌላ የቁም ስቅል የፖለቲካ አዙሪት ውስጥ እንዳይገባ መከላከል፣ በተግባርም ከዛ የጸዳ መሆኑን ማረጋገጥ፣ ለማንም ብለን የምናደርገው ሳይሆን፣ ለራሳችን ብለን፣ በእውነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ የቆምን ስለሆንንና በምንም አይነት እነሱን መምሰል ስለማንፈለግ መሆኑን ለአንድ አፍታም ልንዘነጋው አይገባም::

**ማጠቃለያ**

ውድ ወገኖቼ

ለሃያ ወራት በእስር ያውም በቃሊቲ አይነት እስር ቤት መቆየት፣ ጥሩ ነው፣ ወይንም የአካልና የስነ-ልቦና ጉዳት አያመጣም፣ ስለዚህ ሁሉም ነገር ሰላም ነበር ብዬ ለሞራል ማነቃቂያ እንዲሆን ብነግራችሁ ሃሰት ነው የሚሆነው:: ሌላው ሁሉ ቀርቶ በእዚያ ፍርድ ቤት በየግዜው እየተመላለስን ጥቂት ምንም ይሉኝታ የሚባል ነገር ያልፈጠረባቸው አይን አውጣዎች ፍትህን የመሰለ ነገር እንደዚያ ሲቀልዱበት ማየት ምን ያህል የሚዘገንንና የሚያዋርድ ነገር እንደሆነ ልደብቃችሁ አልችልም:: እዚያ ፍርድ ቤት ስመላለስ ሁል ግዜ ሲሰማኝ የነበረው ሃፍረት በኢትዮጵያዊነቴ ይሰማኝ የነበረው የትንሽነት ስሜት በፍጹም በቃላት ልግልጽላችሁ አልችልም:: አንድ መንግስት የአንድን ሃገር ተቋማት እንዴት ሊያዋርድ እንደሚችል፣ የሶስት ሽህ ዘመን ታሪክ አለን ብለን የምንኩራራ ህዝቦች፣ ከአርባ አመት በፊት ከቅኝ ግዛት ከወጡት አፍሪካዊ ወገኖቻችን ጋር እንኳን ሲነጻጸር እንዴት አሳፋሪ ተቋማት እንዳሉን ማየት ልብ የሚሰብር ነበር:: ይህ መንግስት የፖለቲካ ጥቅም ያገኝ መስሎት የፍትህ ስርአቱን እንደዚህ በአለም ፊት ለትችት ሲዳርገው፣ እራሱንና ሃገሩን እንኳን ምን ያህል እያዋረደ እንደሆነ አልገመተም:: እኛ የዚህ ኢፍትሃዊ ድርጊት ሰለባዎች ለአገራችን የፍትህ ሥርአት ቅሌት ሲሰማን የነበረው የውርደት ስሜት እራስን እንድትጠላ የሚያደርግ ፈታኝ ወቅት እንደነበር አልሸሽጋችሁም:: የዚያኑ ያህል ግን እስር ቤት ሊማር ለፈለገ ብዙ መማር የሚቻልበት ቦታ ነው:: የብዙ እስረኞችን ታሪክ በመስማት በአገራችን ውስጥ ያለውን ቅጥ ያጣ የፍትህ ረገጣ፤ የድህነት መጠን፤ በአጠቃላይ የአገሪቱን ሕዝብ ኑሮ አስቀያሚነት ማየት ይቻላል:: ከሁሉ ባላይ ግን እስር ቤት

ግዜ ይሰጣል። ለማሰብ፣ ለማሰላሰል፣ ያለፉ ሁኔታዎችን መልሶ ለመመርመር ሰፊ እድል ይሰጣል። በግሌ በዚሁ ጊዜ ውስጥ አጥብቄ ያሰብኩበት ነገር ቢኖር ከምርጫ 97 በኋላ ቅንጅት እንደ ድርጅትና የዴሞክራሲ ትግሉ ባጠቃላይ የተጓዘበትን መንገድ ነው። በአቅም ማጣት፣ በድርጅት ብቃት ማነስ---ወዘተ ማድረግ የነበረብን ያላደረግናቸው ነገሮች ይኖራሉ፣ ባለማወቅ የተፈፀሙ ስህተቶች እዚህና እዚያ ሊኖሩ ይችላሉ። ነገር ግን በምንም አይነት የወሰድነውን የፖለቲካ ውሳኔ ስህተት ነው ሊያሰኘን የሚችል ምንም ነገር አላገኘሁም። ትግሉ ለዴሞክራሲ ከነበረ፣ ምርጫን ለዘረፈ መንግሥት ከሰጠነው ባለ 8 ነጥብ የመግባቢያ ሃሳብ ውጭ ልንሰጠው የምንችለው ነገር አልነበረንም። እነኛን ነጥቦች አስቀምጠን ፓርላማ ላለመግባት መወሰናችንም በድርጅታችን ላይ ከደረሰብን በደል ሁሉ በኋላም ትክክል ነበር። ስህተት ቢኖር ለዚያ አይነት የግፍ እርምጃ የሚመጥን ድርጅታዊ ዝግጅት አለማድረጋችን ነበር። በሌላ አነጋገር ያኔ ያደረግነውን የፖለቲካ ውሳኔ አሁን ላይ ሆኘ ስመለከተው አደርገው ነበር? በሚገባ። ያኔም ውሳኔው መሰረት ያደረገው በአገራችን ፍትህና ነፃነት ይከበር፣ ዴሞክራሲን በጋራ እንገንባ ነው። የነፃነት አልባ፣ ፍትህ አልባ የሆነ ኑሮን ከመኖር አሁንም መታሰርን አሁንም መሰደድን ከዚያም በተሻለ ደግሞ አሁንም እስከ መጨረሻው መታገልን እኔም ሆንኩ አብረውኝ የታሰሩት ጓደኞቼ እንመርጣለን። ይህ ነበር የቅንጅት የያኔ አላማ፣ ይህም ነው አሁንም ቅንጅት የሚታገልለት የማያወላዳ አቋሙ።

እውነት ነው የምላችሁ የዴሞክራሲ ትግሉ ባለፈው ሁለት አመት የደረሰበት ችግር፣ የገባበት ውጣ ውረድ ሁሉ ተጨምሮበትም እያሸነፈ እንጂ እያፈገፈገ አይደለም። ዛሬ ከመቸውም በላይ የትግላችን ምንነት ለሁሉም ግልፅ ሆኗል። በዚህ ሂደት ማለፋችን እጅግ አስፈላጊ የሆነ የአላማ ግልፅነትና ፅናት ሰጥቶናል። ዛሬ ከመቸውም በላይ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ የሚኖር ኢትዮጵያዊ ሁሉ ለዲሞክራሲ ትግሉ ተነስቷል። እርግጠኛ ነኝ ከሶስት አመት በፊት በዋሽግተን ዲሲ ኢትዩጵያውያን አካባቢ ስለ አገር ፖለቲካ የሚያወሩ ሰዎች ጥቂት መሆናቸው ብቻ ሳይሆን በተለይ በወጣቱ አይን የሚሰሩት እንዳጡ ሞኞች ይወሰዱ ነበር። ዛሬ የኢትዮጵያ ጉዳይ አይመለከተኝም ብሎ ከዳር ቆሞ ማየት በወጣቶቹም አከባቢ ለከት የሌለው ግለኝነት ብቻ ሳይሆን ዝም ብሎ የፋራነት ምልክት ተደርጎ ሳይወሰድ የሚቀር አይመስለኝም። ትግሉ የጥቂት አዛውንቶች መሆኑ ቀርቶ የሁሉም ኢትዮጵያውያን ሆኗል። አፈናው ከዚህ በፊት በጎሪጥ ይተያዩ የነበሩ የአገር ልጆችን የበለጠ አቀራርቧል። የኢሕአዴግ ፍፁም ኢዴሞክራሲያዊነት ለሁሉም ግልፅ ሆኗል። ባጠቃላይ በአገራችን እውነተኛ ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለማቆም ከመቸውም ጊዜ በላይ የተመቻቸ ሁኔታ ተፈጥሯል። በእያንዳንዱ ቀን ወደዚያ የማይቀር ድል እየተጠጋን ነው። መንገዱ አድካሚ ሊሆን ይችላል። ግን የማይቀር የታሪክ ሂደት ነው። ዋናው ተግባራችን ራሳችን መደራጀት፣ ያልተደራጁትን ማደራጀት፣ የተደራጁትን ሃይሎች ትግል በአንድ ጥላ ስር ማሰባሰብና በጋራ መግፋት ቀጣዩ ስራችን ነው። እንደ ኢትዮጵያውያን ይህን ለማድረግ ብቃቱ እንዳለን ለአንዳፍታም  አልጠራጠርም።

*አመሰግናለሁ።*